# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ


82ኛ ዓመት ቁጥር 150 ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# "በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ያለው ግንኙነት ተጠናክሮ ይቀጥላል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከልዑክ ቡድናቸው ጋር በሮም ጣሊያን ከትናንት ጀምሮ የሥራ ጉብኝት እያደረጉ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያና የጣሊያን ግንኙነት ለብዙ ዘመናት የቆየና ፍሬያማ የሆነ አጋርነት የሚታይበት መሆኑን ገልጸው፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ግንኙነት አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል። በጣሊያኑ ፕሬዚዳንት ሰርጂዮ ማታሬላ ለተደረገላቸው አቀባበልም ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በትናንትናው እለትም ከፕሬዚዳንት ሰርጂዮ ማታሬላ ጋር መክረዋል። ጣሊያን እና ኢትዮጵያ ለረዥም ጊዜ የቆየ እና ታሪካዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የመሠረቱ ሀገራት መሆናቸውንም በዚሁ ወቅት ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፕሬዚዳንት ሰርጂዮ ማታሬላ ጋር ባደረጉት የሁለትዮሽ ውይይት በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል ስላለው ግንኙነት እንዲሁም በሌሎች ወቅታዊ ዓለም አቀፋዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም ሀገራቱ ያላቸውን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት

"በኢትዮጵያና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በወቅቱ ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ሁሉም ርብርብ ሊያደርግ ይገባል

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በወቅቱ ተጠናቀው ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁሉም ርብርብ ሊያደርግ እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጨምሮ የፌዴራል፣ እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በደሴ ከተማ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል።

በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት የተመዘገበበት የደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤትና የወሎ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተጎበኙ መሠረተ ልማቶች መካከል ናቸው።

አቶ ደመቀ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት ትውልድን ለማፍራት የሚሠሩ ትምህርት ቤቶች ላይ መንግሥት በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

የደሴ አዳሪ ትምህርት ቤት እንደ ሀገር ያስመዘገበው ውጤት የሚበረታታ መሆኑን ተናግረው፤ መንግሥት ሀገር ተረካቢ ትውልድ ላይ በትኩረት ይሠራል ብለዋል። በቀጣይ የደሴ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት የተሻለ ሥራ እንዲሠራ አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚደረግለትም ገልጸዋል።

የደሴ ቴሪሸሪ ኬርና ማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ የኀብረተሰቡ ከፍተኛ ፍላጎትና ጥያቄ መሆኑን የገለጹት አቶ ደመቀ፣ የሆስፒታሉ ግንባታ እንዲካሄድ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ከፌዴራል ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መንቀሳቀስ እንዳለበት አመላክተዋል ሲሉ የዘገቡት ኢዜአ እና ኤፍቢሲ ናቸው።


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ







አቶ አለማየሁ ባውዲ

## ሕዝበ ውሳኔው በሰላም ተጠናቀቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ጂንካ ፡- በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች ሲካሄድ የዋለው ሕዝበ ውሳኔ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ መጠናቀቁን በክልሉ በምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ማዕረግ የመልካም

ሕዝበ ውሳኔው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

## "በኢትዮጵያ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እስራኤል ድጋፍ ታደርጋለች"

- አለልኝ አድማሱ
በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር

ገጽ 4








አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት የሚመጥኑ ብቁ መምህራንን ለማፍራት በትኩረት እየተሠራ ነው

ገጽ 3

# "በውሃ እጥረትና ጥራት መጓደል ለችግር ተዳርገናል"

## - በሸገር ከተማ አስተዳደር የሱሉልታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች

# "ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራን ነው"

## - የክፍለ ከተማው ውሃና ፍሳሽ ኢንተርፕራይዝ አገልግሎት

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የሚቀርበው የመጠጥ ውሀ ጥራቱን ያልጠበቀና የሚቆራረጥ በመሆኑ ለችግር መዳረጋቸውን በሸገር ከተማ አስተዳደር የሱሉልታ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ። የክፍለ ከተማው የውሃና ፍሳሽ ኢንተርፕራይዝ በበኩሉ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ፕሮጀክት ነድፎ እየሠራ መሆኑን ጠቁሟል።

የክፍለ ከተማው ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሰዊት ሙሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሱሉልታ ሚዛን አካባቢ ያለው ንጹሕ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት የሚቆራረጥና ጥራቱን ያልጠበቀ ነው። ውሃው ለመጠጥ ግልጋሎት ሲውል ማኀበረሰቡ ከፍተኛ ለሆነ የጤና መታወክ ይጋለጣል። በዚህ የተነሳ ማኀበረሰቡ የከርሰ ምድር ውሀ ቆፍረው ከሚሸጡ የአካባቢው ግለሰቦች እየገዛ መጠቀሙ ለከፍተኛ ወጭና እንግልት ተዳርጓል።

በአካባቢው በቧንቧ የሚቀርበው ውሀ ለመጠጥና የሀበሻ ልብስ ለማጠብ የሚያስችል ጥራት ባይኖረውም ለተለያዩ የቤት ግልጋሎትም ለማዋል የአቅርቦት ችግር እንዳለ የገለጹት ወይዘሮ ሰዊት፤ አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት ሳምንት በላይ ውሀ ሳይለቀቅላቸው እንደሚቆይ ገልጸዋል። የሚመለከተው አካል ያለውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥራቱን የጠበቀ ውሀ ለማኀበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የክፍለ ከተማው ነዋሪ የሆነው ሌላው ወጣት እሸቱ ሰበታ በበኩሉ፤በሱሉልታ ክፍለ ከተማ የውሀ አቅርቦት እጥረት አለ ብሏል።

ወጣት እሸቱ እንዳለው በአካባቢያቸው ውሀ ሳይለቀቅ ከአንድ ወር በላይ ይቆያል፤ የሚለቀቀው ውሀም ጥራቱን ያልጠበቀ በመሆኑ ለመጠጥ ግልጋሎት አይውልም።

በውሀ አቅርቦት እጥረትና በጥራት ጉድለት ምክንያት ለከፍተኛ ወጭና እንግልት መዳረጉን የገለጸው ወጣት እሸቱ፤ የሚመለከተው አካል ጥራቱን የጠበቀ ውሀ ተደራሽ እንዲሆን በትኩረት ሊሠራበት ይገባል ሲል ጠይቋል።

የአካባቢው ነዋሪ የሆኑት አቶ ሳሙኤል አበበ በተመሳሳይ በሰጡት አስተያየት፤ የውሀ አቅርቦት እጥረት ከመኖሩም ባሻገር የሚቀርበው ውሃ ጥራት የሌለው በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪ ለተለያዩ የውሀ ወለድ በሽታዎች እየተጋለጠ ነው ብለዋል፡፡

ውሀ ሳይለቀቅላቸው ከወር በላይ እንደሚቆይ እና ለመጠጥና ለተለያዩ የቤት ግልጋሎት የጉድጓድ ውሀ ከሚሸጡ ግለሰቦች እየገዙ በመጠቀማቸው ለችግር



እየተጋለጡ መሆኑን አንስተዋል የሚመለከተው አካል መፍትሔ እንዲሰጥ ጠይቀዋል።

ኢፕድ ለነዋሪዎች ቅሬታ ምላሽ እንዲሰጡ ያነጋገራቸው የሱሉልታ ክፍለ ከተማ የውሃና ፍሳሽ ኢንተርፕራይዝ አገልግሎት ኃላፊ አቶ ገመቹ መኮንን፤ በከተማዋ የንጹሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና የጥራት ችግር መኖሩን ተናግረዋል።

በክፍለ ከተማው ያለውን የንጹሕ ውሃ አቅርቦት ችግር በመቅረፍ የተጣራና ለመጠጥ የሚውል ውሃ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የንጹሕ መጠጥ ውሀ አገልግሎት እንዲሰጥ ተቆፍሮ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየው ጉድጓድ ለተለያዩ ችግሮች መጋለጡን የጠቆሙት አቶ ገመቹ፤ የውሃውን ንጽሕና የሚያጣራ ማሽን ለመግዛት በግዢ ሂደት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሆኖም ግዥው በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት መዘግየቱን ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት የኅብረተሰቡን የንጹሕ መጠጥ ውሃ ችግር መቅረፍ የሚችል ሌላ የውሃ ፕሮጀክት መጀመሩን ጠቁመዋል። ይህም በሦስት ወራት ውስጥ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር ጠቁመዋል።

ከተሞቹ ቀደም ሲል ዓመቱን ሙሉ ውሃ የሚያገኙ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ገመቹ፤ የተነሳው የውሃ አቅርቦት እጥረት ቅሬታ የተከሰተው አገልግሎት እየሰጠ የነበረው ጉድጓድ የውሃ እጥረትና ያልታወቀ የቴክኒክ ችግር ስለገጠመው እንደሆነም አብራርተዋል።

ያም ሆኖ ግን ከአገልግሎት አንጻር የሚከሰተውን የውሃ እጥረት ለመቅረፍ በአራት ሽፍት በመከፈል ሁሉም ቢያንስ በሳምንት አንዴ ውሀ እንዲያገኙ ይደረጋል ብለዋል።

በአጠቃላይም ከሦስት ወር በኋላ አገልግሎት የሚሰጠው አዲሱ የሱሉልታ የውሃ ፕሮጀክት ግልጋሎት እስኪሰጥ ድረስ ማኀበረሰቡ በመታገስ ያለውን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በቅንጅት መሥራት ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

# በቀጣዮቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቃማ የአየር ሁኔታ ይጠበቃል

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- የየካቲት ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የአየር ሁኔታው ደረቃማ እንደሚሆን ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ምክር አገልግሎትና ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አሳምነው ተሾመ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ በየካቲት ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የአየር ሁኔታው ደረቃማ ይሆናል።

በዚሁ መሠረት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቃማው የአየር ሁኔታ አመዝኖ የሚቆይ ሲሆን ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ያላቸው የሚትዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂና ቦረና ዞኖች ቀላል ዝናብ ይኖራቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚገኙ የቤንች ማጂ፣ ሀዲያ፣ ወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞና ጎፋ ዞኖች፤ ሰገን ሕዝቦች፤ ከደቡብ ምዕራብ ክልል የከፋ ዞን፤ ሲዳማ ክልል ቀላል ዝናብ ያገኛሉ።


አቶ አሳምነው ተሾመ አክለው፣ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን ሦስትና አምስት፤ ከትግራይ ክልል የምሥራቅ ዞን ቀላል ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል ሲሉም አመላክተዋል።

የአሥሩ ቀናት የአየር ሁኔታ አዝማሚያው በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ መደበኛ መሆኑን ያወሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተወሰኑ የደቡብ ምዕራብና የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው ብለዋል።

የካቲት ወር በሌሎቹ የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ለበልግ ሥራ እንቅስቃሴ ዝግጅት የሚጀምሩበት ጊዜ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በትንበያው መሠረት የወሩ የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር እንደሚኖራቸውና በአንዳንድ ሥፍራዎች የተወሰነ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል።

አነስተኛ እርጥበቱን በመጠቀም የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የበልግ ወቅት ሰብሎች አስቀድሞ በሚዘራባቸው አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅት፣ ዘር ለመዝራትና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት አቅርቦት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል ብለዋል።

ወቅቱ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች እርጥበት ማግኘት የሚጀምሩበት ወቅት ነው ያሉት አቶ አሳምነው፤ በታችኛው አዋ ጊቤ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ አዋሳኝ ተፋሰሶችና በጥቂት የታችኛው የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል ብለዋል።




ጭሮ ኢንዱስትሪ ዞን ዲዛይን

# በኦሮሚያ ለ75ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ አምስት የኢንዱስትሪ ዞኖች ሊገነቡ ነው

## - ለግንባታው በተለዩት አምስት ከተሞች 400 ሄክታር መሬት ተዘጋጅቷል

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ ፡- ለ75ሺህ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ኢንዱስትሪ ዞኖች በአምስት ከተሞች ለመገንባት የከተሞች ልየታ ማድረጉን ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ ። ለግንባታው ከተለዩት አምስት ከተሞች 400 ሄክታር መሬት መቅረቡን እና የልየታ ጥናቱ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን መካሄዱም ተገልጿል።

በኢንዱስትሪ ዞን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ዙሪያ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት የአዳማ ዩኒቨርሲቲ ምጣኔ ሀብት ባለሙያ እና ተመራማሪ ዶክተር ዑመር በሪሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ ክልሉ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ለማጠናከር በአምስት ከተሞች ኢንዱስትሪ ዞኖችን ለመገንባት እየተንቀሳቀሰ ነው። ኢንዱስትሪ ዞኑ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ ለ75ሺህ ዜጎች ሥራ በመፍጠር ጉልህ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያ ጠቀሜታ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ።

በኢንዱስትሪ ዘርፍ እንደ ሀገር ከተጀመረው ተሞክሮ መሠረት በማድረግ በክልሉ ለማስፋት የታለመ ሲሆን ልየታው ሦስት ጉዳዮችን ማለትም የግንባታ ዲዛይን፣ማኀበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፣ ከአካባቢና አየር ብክለት አንጻር እንዲሁም የመንግሥት እና የኅብረተሰቡ ፍላጎት ላይ ትኩረት በማድረግ መካሄዱንም ጠቁመዋል።

ከቅርበት አንጻር ጭሮ ከተማ ለውጪ ሀገር ገበያና ለባቡር ትራንስፖርት ያለውን ቅርበት ፣ ያቤሎ ከተማ ወደ ኬንያ ወደብ ያለውን ቅርበት እንዲሁም ሰንዳፋ ፣ አምቦ እና ተፍኪ በመሐል ከተማ ለሚገኘው ለአየር ማረፊያ ያላቸው ቅርበትን ግምት ውስጥ በማስገባት ለግንባታው መለየታቸውን ገልጸዋል።

የኢንዱስትሪ ዞን ግንባታው ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል ያሉት ዶክተር ዑመር፤ መንግሥት የኅብረተሰቡን ፍላጎት በተቀናጀ መልኩ ወደ ሥራ ለማስገባት ለሚደርገው ጥረት የሚያግዝ መሆኑንና ከዚህም በመነሳት ለኢንዱስትሪ ዞኑ ግብዓት የሚሆኑ በአካባቢው የሚገኙ ጥሬ ሀብቶች መሠረት በማድረግ የገበያ ትስስር የሚፈጠርባቸው መንገዶችን በጥናቱ ተካትተዋል ብለዋል ።

የኢንዱስትሪ ዞኖቹ ግንባታ በአካባቢው የሚገኝ ምርት በቴክኖሎጂ በመታገዝ እሴት በመጨመር የአካባቢውን ኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ በማድረግ፤ የገበያ ትስሰርን በማጠናከር፤ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በመተካትና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት አቅማቸው የጎላ ነው ብለዋል ።

በግንባታ ወቅትና ከግንባታ በኋላ ቋሚና ጊዜያዊ ሥራዎች በመፍጠር ገጠርና ኢንዱስትሪን በማስተሳሰር ወደ ከተማ የሚፈልሰው ወጣት በአከባቢው ባለሙያ ሆኖ ሕይወቱን የሚመራበት ሁኔታዎችም ይፈጠራሉ ነው ያሉት።

ለግንባታው 400 ሄክታር መሬት መቅረቡ፣ ለካሳ ክፍያ እና ግንባታ ክፍያ ብዙ ወጪ ስለሚጠይቅ የፋይናንስ አቅርቦት በመንግሥት እንዲመቻች በጥናቱ መለየቱን ያብራሩት ዶክተር ዑመር፤ ከሀገር ውስጥ ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ድረስ ያሉ ፋይናንስ ተቋማት የሚገኝ ገንዘብም በረጅም ጊዜ ብድር እንደመፍትሔ ጥናቱ ዳስሷል። ልማት የሚያግዙ እንደ አፍሪካ ልማት ባንክ እንደምሳሌ በመጥቀስ መንግሥት ከ15 እስከ 20 ዓመት ብድር በማመቻቸት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚችል ገልጸዋል ።

በካሳ ክፍያ አርሶ አደሩን ከቦታው ሳያፈናቅል ሥራ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ተያይዘው የሚያድጉበት ሁኔታ በመፍጠር ኢኮኖሚ ሽግግር እውን እያደረገ በመጀመሪያው አምስት ዓመት ለ75ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም ይኖረዋል ።

ሼዶች በመሥራት እንዲሁም በተሠራው ውስጥ በማምረት በሁለት መልክ የግል ባለሀብቶች መሳተፍ እንደሚቻልና መንግሥትና ኅብረተሰብ ተባብረው እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል ።

ዜና

# ሠራዊቱ ሙያዊ አቅምን በማጎልበት ማንኛውንም ጥቃት መመከት በሚያስችል ዝግጁነት ላይ ይገኛል

ጌትነት ተስፋማርያም


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት ሙያዊ አቅምን በማጎልበት ማንኛውንም ጥቃት መመከት በሚያስችል ዝግጁነት ላይ መሆኑ ተገለጸ። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት የስድስት ወራት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ውይይት አካሂዷል።

የመከላከያ ፋይናንስ ሥራ አመራር ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ ወይዘሮ ማርታ ሉዊጂ ባቀረቡት ሪፖርት፤ መከላከያ ሚኒስቴር ባለፉት ስድስት ወራት ሁሉንም አደረጃጀቶች በአቅም፣ በጥራትና በቴክኖሎጂ አቅም የማጠናከር ሥራ መሥራቱን ገልጸዋል።

የምድር ኃይልን በሰው ኃይልና የውጊያ አፈጻጸም በማጎልበት ከአየር ኃይልና ከሌሎች አቅሞች ጋር ያለውን ቅንጅት የማሳደግ ዕድል ተፈጥሯል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሠራዊቱ ሙያዊ አቅምን በማጎልበት ማንኛውንም ጥቃት መመከት በሚያስችል ዝግጁነት ላይ ይገኛል ብለዋል።

የመከላከያን አጠቃላይ ዝግጁነት በማሻሻል ጦርነትን ቀድሞ የመከላከል አቅም መገንባት ተችሏል። የመዋቅራዊ ሪፎርሙን የማጠናከር ሥራም በቀጣይ ጊዜያት ተጠናክሮ በዘላቂነት ይከናወናል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢፌዲሪ መከላከያ ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ ዶክተር አህመዲን መሃመድ በበኩላቸው፤ መከላከያ በትጥቅና በመረጃ ግንኙነት አቅም እንዲያድግ በማድረግና ከተለያዩ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ እንዲሠራ በማድረግ የታየው ልምድ ውጤታማ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲና ከተለያዩ የደህንነትና የጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የባሕር ኃይልን አቅም የማሳደግና የሳይበር ጥቃት ዝግጁነት /የሳይበር ዋርፌር/ ብቃትን የማሳደግ ሥራ በስድስት ወራት ውስጥ መከናወኑን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር አህመዲን ማብራሪያ፤መከላከያ ከአገር ውስጥ ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ እንዲሠራ ከማድረግ ባለፈ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና የተለያዩ አገራት ጋር በስምምነት የሚሠራባቸው መንገዶች ተመቻችተዋል።

በቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ፣ በመከላከያ ምርምር ሥራዎች፣ በባሕር ኃይል ዝግጁነትና በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የአገር መከታ የሆነውን መከላከያን ጠንካራ አቅም እንዲፈጥር የሚደረገው ጥረት በመልካም መንገድ ላይ ይገኛል። ይህ ተቋማዊ አቅም የመገንባት ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል ሲሉም አስታውቀዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ነገዎ በበኩላቸው ፤ የመከላከያ ሠራዊትን አጠቃላይ አቅም በማሳደግ ረገድ የተከናወኑ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ መደረጉ የሚያስመሰግን ነው ብለዋል።

መከላከያ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የተቃጡ ውስብስብ ጥቃቶችን እየመከተ እራሱን የማደራጀትና የልማት ሥራዎችን በተጓዳኝነት ያከናወነበት መንገድ የሚበረታታና መቀጠል ያለበት ክንውን መሆኑን ተናግረዋል።

በውይይቱ ወቅት በቀረበው ሪፖርት መሠረት፤ መከላከያ የራሱ የሆነ አርሚ ባንክ ለማዋቀር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

በመከላከያ አርሚ ፋውንዴሽን በኩል ለማቋቋም የታቀደው የአርሚ ባንክ አዋጭነት ጥናት መካሄዱን የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሉዊጂ አስታውቀዋል።

# ኢትዮቴሌኮም `ኢትዮቴል ኢኖቬሽን' የተሰኘ አዲስ መርሐ ግብር አስጀመረ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያስችል « ኢትዮቴል ኢኖቬሽን» የተሰኘ ጀማሪ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ ቢዝነሶችና ባለሙያዎች የሚበረታቱበት መርሐ ግብር አስጀመረ። መርሐ ግብሩ ለ250 ጀማሪ ኩባንያዎች ዕድል እንደሚሰጥም አስታውቋል።

"ኢትዮቴል ኢኖቬሽን ፕሮግራም" የተሰኘ አዲስ መርሐ ግብር ትናንት ሲጀመር የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ፤ መርሐ ግብሩ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ወሳኝ ነው ብለዋል። ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እንደገለጹት፣ መርሐግብሩ የአገሪቱን ጀማሪ ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረጉ ቢዝነሶችና ባለሙያዎች የሚበረታቱበት ሲሆን፤ ጀማሪ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሠማሩ ተቋማትን የሚያበረታታና የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈታ ነው። ከዚህም ባሻገር ለማኅበረሰቡ መፍትሔ የሚሰጥ ነው።

የቴሌኮም ዘርፉ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትብብር የሚጠይቅ መሆኑን የጠቆሙት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ኢትዮቴል ኢኖቬሽን ፕሮግራም የተቋማትን ትብብርን የሚያበረታታ መርሐ ግብር ነው ብለዋል። መርሐ ግብሩን ለማስጀመር የቴሌኮም መሠረተ ልማትን የሚሟላት አስቻይ ሁኔታ መፈጠሩንም ገልጸዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ኢትዮ ቴሌኮም በሚሰጠው አገልግሎት የአገራችንን ሁለንተናዊ እድገት ለመደገፍና የአስቻይነት ሚናውን ለመጫወት በየጊዜው አዳዲስ አገልግሎቶችን በተለይም የዲጂታል መፍትሔዎች ላይ በማተኮር በትኩረት እየተሠራ ነው።

ኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎቱን ለማስፋፋትና ለማዘመን ከሚያደርገው ዘርፈ ብዙ ጥረቶችና ሥራዎች ባሻገር አገር በቀል ቴክኖሎጂዎችንና ሥራ ፈጠራን ለማበረታታት ያለመ «ኢትዮቴል ኢኖቬሽን ፕሮግራም» የሚል የኢትዮጵያን ጀማሪ የዲጂታልና የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ቢዝነሶችንና ባለሙያዎችን የሚያበረታታና የሚያግዝ ፕሮግራም መጀመሩ ፋይዳው ለሀገር ላቅ ያለ ነው ብለዋል።

መርሐ ግብሩ ማንኛውም ጀማሪ የንግድ እንቅስቃሴ ሊገጥመው የሚችለውን ወደ ገበያ ዘልቆ የመግባት፤ ደንበኛ የመሳብና የመያዝ፤ የባለሙያና የገንዘብ እጥረት ተግዳሮቶችን በመፍታት ጅምር የቢዝነስ ሀሳቦችን ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማብቃት የሚያስችል እንደሆነ ሥራ አስፈጻሚዋ ጠቁመዋል።

ፕሮግራሙ የተጀመሩ ቢዝነሶችን ለማሳደግ ታልሞ በሦስት ምዕራፎች ተከፍሎ የተቀረጸ ሲሆን መሠረታዊ ዓላማው የሀገር በቀል ችግር ፈቺ ተግባራትን ማበረታታት፤ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች መሳብ፤ ማነሳሳትና አዳዲስ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ማገዝ፤ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የፈጠራ ሀሳቦችን እንዲያጎለብቱና አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ወደ ገበያ እንዲያመጡ መደገፍ ነው።

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፤ የተጀመረው መርሐ ግብር የማርኬቲንግ፤ የተለያዩ ሥልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ ድጋፎች የሚገኙበት ሲሆን የዘርፉን ሥነ ምሕዳር በመገንባት ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ወደ ገበያ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ድጋፍ የሚያገኙበት መሆኑን ጠቁመዋል። የሽርክና ንግድ አማራጮች የሚያገኙበትን ሁኔታም ያመቻቻል ሲሉ ገልጸዋል።

የመርሐግብሩ መጀመሪያ ምዕራፍ ከየካቲት 03 እስከ ሚያዚያ 22 ቀን 2015 ዓ.ም የሚከናወን ሲሆን ትኩረቱም በጀማሪ የክላውድና የሞባይል ፋይናንስ ቢዝነሶች ላይ ነው" ይህ ምዕራፍ ተወዳድረው የሚያሸንፉ 100 ተወዳዳሪዎች ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶችና እጥረቶችን የሚፈቱበትና ንግዳቸውን በስኬት የሚያስቀጥሉበት እንዲሁም ለተግባር የቀረቡ ጅምር የፋይናንስና ክላውድ ቢዝነስ ሀሳቦች በፍጥነት ወደ ሥራ የሚገቡበት ፕሮግራም ስለመሆኑ ሥራ አስፈጻሚዋ ተናግረዋል።

ተወዳድረው የሚመረጡት 100 አሸናፊዎች ሙያዊ ምክርን ጨምሮ የባለሙያ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅርቦቶችን የሚያገኙ ሲሆን ከሁዋዌ ቴክኖሎጂ ጋር በመተባበር ወደ ቻይና ሀገር ተጉዘው ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመመልከት ልምድ የሚካፈሉበትንም እድል ያመቻቻል።

በኢትዮቴል ኢኖቬሽን ፕሮግራም የመጀመሪያው ምዕራፍ መወዳደር የሚፈልጉ የክላውድ እና የሞባይል ፋይናንስ ጀማሪ ቢዝነሶች በኢሜይል አድራሻ ethiotelinnovation@ethotelecome ላይ ከየካቲት 3 እስከ መጋቢት 3 ቀን 2015 ዓ.ም ማመልከት የሚችሉ መሆኑንም ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ጠቁመዋል።

# አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት የሚመጥኑ ብቁ መምህራንን ለማፍራት በትኩረት እየተሠራ ነው

ፋንታነሽ ክንዴ


ዶክተር ሙሉቀን ንጋቱ

አዲስ አበባ፡- አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት የሚመጥኑ ብቁ መምህራን ለማፍራትና የነባሮቹን አቅም ለማጎልበት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና ትምህርት አመራር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሙሉቀን ንጋቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ተግባራዊ የተደረገውን አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት እውን ለማድረግ የመምህራን ሚና የጎላ ነው። በመሆኑም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመምህራንን ብቃት ለማሳደግ በልዩ ትኩረት እየሠራ ነው።

የመምህራን ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ መምጣቱን በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ ያሉት ዶክተር ሙሉቀን፤ በተጨማሪም በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የተጨመሩ ተግባር ተኮር የትምህርት አይነቶችን የሚያስተምሩ የመምህራን እጥረት አጋጥሟል ብለዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ብቃት ያላቸውን መምህራን ለማፍራት ከሥርዓተ ትምህርት ማሻሻል ጀምሮ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሠራ ነው ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ የተለወጠውን ሥርዓተ ትምህርት የሚመጥን የመምህራን ማሰልጠኛ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የተካተቱ የትምህርት አይነቶችን ያካተተና መምህራንን ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የበለጠ እንዲተዋወቁ የሚያደርግ ተከታታይነት ያለው የሙያ ማሻሻያ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑንም አክለው ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አዳዲስ መምህራንን ለማፍራት ከሚያደርገው ሥራ ጎን ለጎን በሥራ ላይ ያሉ መምራንን አቅም ለማጎልበት ባለፉት ዓመታት የመምህራን የሙያ ብቃት ምዘና ሲሰጥ መቆየቱን ያወሱት ዶክተር ሙሉቀን፤ አሁን ግን አሠራሩን ማዘመንና ከሲቪል ሰርቪስ ሥርዓቱ ጋር አብሮ በመሥራት ከደረጃ እድገት መሰላሉ ጋር ለማያያዝ ታስቦ ጭምር መሆኑን አብራርተዋል።

አሠራሩ ላይ ክለሳ በማድረግ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር የሥራ ክፍሉን ለማቋቋምና ምዘናው በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጥ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ባለፉት ዓመታት 10ኛ ክፍል አጠናቀው የማለፊያ ነጥብ ያላመጡ ተማሪዎች ወደ መምህርነት እንዲገቡ ሲደረግ መቆየቱ ለትምህርት ጥራት መውረድ ትልቅ ሚና መጫወቱን አስታውሰው፤ ከዚህ በኋላ በትምህርቱ ዘርፍ የልህቀት ማዕከላት ተደርገው የመምህርነት ፍላጎት ያላቸውና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፈርት የተለዩ ተማሪዎች ብቻ ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል።

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ዶክተር ደጀን ጫካ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሆኖ በዘርፉ ለሚስተዋሉ ችግሮች የመፍትሔ አካል እንዲሆን ኃላፊነት ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ የሥልጠና ፍኖተ ካርታና ሥርዓተ ትምህርት ከማዘጋጀት ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህንም ተከትሎ በሥራ ላይ ያሉ መምህራንን አቅም ለማጎልበትና አዳዲስ ሠልጣኞችንም ለማፍራት አስፈላጊው ዝግጅት ማድረጉን አንስተዋል።

አሁን ላይ በአዲሱ ሥርዓት ትምህርት የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞችን ተቀብሎ ማስተማር መጀመሩን ጠቅሰው፤ በቀጣይነትም ከማስተማር ባለፈ አስፈላጊ ሆኑ ሥርዓተ ትምህርቶችን መቅረጽ፣ ዘርፉን መምራት፣ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ የዘርፉ ችግሮችን መቅረፍ የሚችሉ ሙያተኞችን ለማፍራት እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

አሁን ላይ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲውን ተቀላቅለው የመጀመሪያ ዓመት ትምህርቶችን ከተከታተሉ በኋላ መምህርነትን የመረጡ ተማሪዎችን እያሰለጠነ መሆኑን አስታውሰው፤ ወደፊት ተማሪዎችን በብቃታቸው በፍላጎታቸው አወዳድሮ ለመቀበል ማቀዱን ጠቁመዋል። ለዚህም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል መዘጋጀት የሚገባቸውን የሕግ ማዕቀፎች እየጠበቀ መሆኑን ገልጸዋል።

ለጥረቱና ለትምህርት ጥራቱ ውጤታማነት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲሁም መገናኛ ብዙኃንም የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጠይቀዋል።

# "በኢትዮጵያና በጣሊያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይበልጥ በሚያጠናክሩበት አግባብ ላይ መወያየታቸውንም ጠቁመዋል።

በተያያዘም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ከጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ ጋር ተወያይተዋል።

በውይይታቸውም በሁለቱ ሀገራት ትብብር እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ የ180 ሚሊየን ዩሮ የገንዘብ ድጋፍ የያዘውን የ2023-2025 የኢትዮጵያ እና የጣሊያን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ተፈራርመዋል።

የፋይናንስ ስምምነቱ በኢኮኖሚ ልማት በተለይ በግብርና እና በኢንዱስትሪ ዘርፎች እና በጤና እና በትምህርት መሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት፣ ቁልፍ በሆኑ ተግባራት ላይ እንደሚውል ተገልጿል።

ስምምነቱ ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም እና የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድን ለማስቀጠል የሚደግፍ መሆኑም ተጠቁሟል።

ሁለቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ትብብራቸውን የበለጠ ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቀዋል።

# ሕዝበ ውሳኔው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አስተዳደር ክላስተር አስተባባሪና የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ አለማየሁ ባውዲ አስታወቁ።

አቶ ዓለማየሁ ባውዲ ሕዝበ ውሳኔው በሰላም መጠናቀቁን ተከትሎ በጂንካ ከተማ ትናንት መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸው እንዳስታወቁት የሚተዳደሩበትን የክልል አደረጃጀት ለመወሰን በዞኖቹ እና በልዩ ወረዳዎቹ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት በሰላም ተጠናቋል።

ሕዝበ ውሳኔው በተካሄደባቸው ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች በተቋቋሙ 3 ሺህ 771 የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ የመስጠቱ ሂደት ከማለዳው 12:00 እስከ ምሽቱ 12:00 ድረስ ተካሂዶ በሰላም ተጠናቋል።

የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሕዝቡ ከፀጥታ ኃይሉ ጋር በመተባበር ያሳየው ቁርጠኝነትና ጨዋነት የሚመሰገን እንደሆነ ተናግረዋል።

አክለውም የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም እንዲጠናቀቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ አካላትን አመስግነዋል።

በተለይ ኅብረተሰቡ ለአካባቢው ሰላም ግንባር ቀደም ተሰላፊ በመሆን ያደረገው ተሳትፎ ሕዝበ ውሳኔው ያለምንም ስጋትና እንከን በሰላም እንዲጠናቀቅ አስችሏልም ብለዋል።

ሕዝበ ውሳኔው በሰላም መጠናቀቅ ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በመሆን አስተዋጽኦ ያደርጉ አካላትን፣ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ምርጫ አስፈፃሚዎችና ታዛቢዎች ምስጋና አቅርበዋል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።

# "በኢትዮጵያ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እስራኤል ድጋፍ ታደርጋለች"

\- አለልኝ አድማሱ
በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የእስራኤል መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አስታወቁ።

በኢትዮጵያ የእስራኤል አምባሳደር አለልኝ አድማሱ በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት የመንግሥትና የሕዝብ ትኩረት በሰሜኑ የሃገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ላይ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህን ከባድ ፈተና አልፎ ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ ልማቱ የሚመልስበት ጊዜ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፤ እስራኤልም የሚያስፈልገውን ድጋፍ ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ናት።

በቅርቡ የተጀመረው የበጋ ስንዴ ምርት የሚደነቅ መሆኑን የተናገሩት አምባሳደሩ፤ መሬት ያለ እረፍት ለሕዝቦች ምርት መስጠት እንዳለበት ጠቁመው፤ የሀገር ኢኮኖሚ የሚያድገው መሬት ጦም እንዳያድር በማድረግ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች፣ ሰፊ የቆዳ ሃብት እና በቂ የሰው ኃይል ያላት በመሆኑ በአጭር ጊዜ ወደ ሥልጣኔ መምጣት የምትችል መሆኑን ገልጸው፤ በእስራኤል ሀገር ከፍተኛ ሀብት የሚያንቀሳቅሱት የተለያዩ የግል ድርጅቶች ወደኢትዮጵያ መጥተው በቴክኖሎጂና በዕውቀት እንዲደግፉ ለማድረግ እስራኤል ትሠራለች ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ የእስራኤል አልሚ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል። ትልቅ አቅም ያላቸው ድርጅቶች በእስራኤል ያሉ በመሆኑ በኢትዮጵያ መሥራት ይፈልጋሉ፤ ለዚህም የሚሆን የማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጠንካራ ግንኙነት አለ።

ከኢትዮጵያ በኩልም የተፋጠነና ምቹ የአሠራር ሂደትን በመፍጠር የውጭ ኩባንያዎች ወደሀገር እንዲመጡ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የእስራኤል የቆዳ ስፋት ጠባብ ቢሆንም ቴክኖሎጂን በመጠቀም በአሸዋ ላይ ከፍተኛ የሆነ ምርት ታመርታለች ያሉት አምባሳደር አለልኝ፤ ይህ ወደ ኢትዮጵያ እንዲስፋፋ እስራኤል ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ተናግረዋል።

ወቅትን በመጠበቅ ሳይሆን ቴክኖሎጂን በመጠቀም በሁሉንም ወቅቶች በምርምር ተደግፎ ማምረት እንደሚገባ እና ኢትዮጵያ ከጀመረችው የበጋ ስንዴ ግብርና ትምህርት በመቅሰም ሌሎችንም ሰብሎች በስፋት ማምረት ትችላለች ብለዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና እንዲዘምን እስራኤል ብዙ ሥራዎችን እየሠራች ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ እስራኤል ከአራት ሚሊዮን በላይ የአቮካዶ ችግኞችን ለኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በማሰራጨት በስፋት እየተመረተ መሆኑን አስረድተዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢኮኖሚ ስብራቱ እየታከመ ያለበት መንገድ የሚበረታታና ዘላቂ የኢኮኖሚ ድል ለማስመዝገብ የሚያስችል ነው!

ከለውጡ በፊት የነበረው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስብስብ በሆኑ ችግሮች የተያዘ፤ ሀገርን እንደሀገር የከፋ የህልውና አደጋ ውስጥ ሊከት በሚያስችል ቁመና ላይ እንደነበር ይታወቃል፤ ከለውጡ ዋነኛ ገፊ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው ይኸው በኢኮኖሚው ዘርፍ የነበረው ሀገራዊ ስብራት መሆኑም ይታመናል።

በመንግስት መዋቅር እስከ መደገፍ የደረሰ የከፋ ሙስና ፣ የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ሳይቀሩ የሚሳተፉበት የኮንትሮባንድ ንግድ ፣ ምርት ላይ ሳይሆን ብድር ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ መንገድ፣ የዓባይ ግድብን ጨምሮ የነበሩ የፕሮጀክቶች መዘግየትና ጥራት መጓደል፣ በተለያየ ጊዜ የተወሰደና ሲንከባለል የመጣው ከፍተኛ የሀገር ዕዳ፣ ከሀገር በስፋት ሲሸሽ የነበረ ሀብት ወዘተ ለሀገራዊ ኢኮኖሚው ስብራት ተጠቃሽ ምክንያቶች ነበሩ።

በወቅቱ አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከውጪ ምንዛሬ እጥረት ጋር በተያያዘ በሙሉ አቅም ማምረት አለመቻላቸው ፤በምርት ሂደት ውስጥም ያሉት ቢሆኑ በሰላም እጦት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ከምርት ውጪ መሆናቸው፤ የሀገራዊ የኢኮኖሚ ስብራቱ መገለጫ እንደነበሩ ይታወሳል።

ሀገርን እንደ ሀገር ለማስቀጠል የሚያስችል የውጪ ምንዛሬ ክምችት አለመኖር፤ መንግስት መንግስታዊ ስራውን ማከናወን የሚያስችል በቂ ሀብት በእጁ አለመኖሩ፤ ከዚያም ባለፈ በተጠና እና በተናበበ መንገድ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ሲደረጉ የነበሩ አሻጥሮች ሌሎቹ የስብራቱ ማሳያ ነበሩ።

ይህን ተጨባጭ ተግዳሮት ሰብሮ ለመውጣት የለውጥ ኃይሉ /መንግስት/ አዲስ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ከማድረግ ጀምሮ ስትራቴጂክ በሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ፈጣን የማሻሻያ ርምጃዎችን በመውሰድ ሀገርን ከፍ ካለ ውድቀት መታደግ ችሏል።

በተለይም እንደ የዓባይ ግድብን የመሳሰሉ ሀገራዊ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ችግሮች ፈጥኖ በማጥናትና ፕሮጀክቶቹ ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚቀጥሉበትን አዲስ የቁጥጥርና የክትትል ስርአት በመንደፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲያገግም ማድረግ የሚያስችሉ ተጨባጭ ተግባራትን አከናውኗል።

በመንግስት መዋቅር ሲካሄዱ በነበሩ የሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ላይ የማያዳግም እርምጃ ወስዷል፤ ለከፍተኛ ሙስና የተጋለጡ ተቋማትን በመለየትም በአዲስ አደረጃጀትና አመራር ተስፋ ሰጪ ወደ ሆነ ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ ማድረግ ችሏል።

ኢኮኖሚው በአንድ ወይም በሁለት ዘርፎች ሳይታጠሩ ዘርፈ ብዙ እንዲሆኑና በብዙ ተግዳሮት ውስጥ የነበረው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚነቃቃበትን የተለያዩ አማራጮች በመጠቀም ኢኮኖሚው መንግስት ተገዶ የገባበትን ጦርነት መሸከም የሚያስችል አቅም እንዲፈጥር አድርጓል። በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት የተመሰከረለትን ዕድገትም በየዓመቱ እያስመዘገበ እንዲሄድ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ችሏል።

በእርግጥ ሀገራዊ ኢኮኖሚያቸው ረጅም መንገድ የተጓዘ ችግር ውስጥ ያሉ ሀገራት፤ ኢኮኖሚያቸውን ከውድቀት ታድገው ከፍያለ ሀገራዊ አቅም ለመገንባት የሚያደርጓቸው ጥረቶች በአንድ ምሽት ተጀምረው የሚያበቁ አይደሉም። የትናንት ስብራቶቻቸውን በሚገባ ተረድተው በአግባቡ ማከምን የሚጠይቅ ነው።

ከዚህ አንጻር መንግስት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ስብራት በአግባቡ አጥንቶ ስብራቱን ለመፈወስ እየሄደበት ያለው መንገድና የሚጓዝበት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ እሴቶች የሚበረታቱና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ድል ለማስመዝገብ መሰረት እየጣሉ ያሉ ናቸው።

ከዚህ አንጻር መንግስት ሰሞኑን ዓለምአቀፉ የገንዘብ ድርጅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያድግበታል ብሎ ያስቀመጠው የትንበያ ውጤት፤ተስፋ ሰጪ ነው፤ በቀጣይ የተጀመረው ሀገራዊ የሰላም ጥረት ተጨባጭ ፍሬ ሲያፈራ እውነታው ከዚህ የተለየ ገጽታ ሊኖረው እንደሚችልም ይታመናል።

ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አኳያም ቢሆን ሀገሪቱ ካለችበት የተመራጭነት ደረጃ አንጻር፤ በቀጣይ ሊኖር የሚችለው የዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንት ፍሰት ዓመታት ያስቆጠረውን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ስብራት ለማከም ትልቅ አቅም እንደሚሆንም አያጠራጥርም።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

# የትምህርት ስርዓቱን ስብራት የጠቆመው የፈተና ውጤት

ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ

የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ውጤት ከቀናት በፊት ይፋ መደረጉ ይታወሳል:: የትምህርት ሚኒስቴር በገለፀው መሰረት፣ ፈተናውን ከወሰዱ 899ሺ520 ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ ውጤት (ከ350 በላይ) ማስመዝገብ የቻሉት 29ሺ909 (3.3%) ብቻ ናቸው:: ከ50 በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ አዲስ አሰራር ለመከተል መታቀዱንም ሚኒስቴሩ ገልጿል::

በዚህ አሰራር ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተው የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ይሆናሉ፤ቀሪዎቹ ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎችን የመቀበል አቅም መሰረት በማድረግ የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ተመርጠው ወደ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲገቡ ይደረጋል፤ይሁን እንጂ እነዚህ ተማሪዎች በቀጥታ የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አይሆኑም፤ተማሪዎቹ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡባቸውን የትምህርት ዓይነቶች ለአንድ ዓመት በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እየተማሩ ከቆዩ በኋላ፣ በዓመቱ መጨረሻ ፈተና ተፈትነው ካለፉ በዩኒቨርሲቲዎች የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ሆነው ይቀጥላሉ::

ውጤቱ ይፋ ከተደረገ በኋላ ብዙ ዓይት አስተያየቶችን አስተናግዷል:: አንዳንዶች ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ የትምህርት ጥራት አለመኖሩን የሚያመለክት እንደሆነ ሲገልፁ፣ ሌሎች ደግሞ ‹‹የፈተና ስርዓቱ ኩረጃንና ሌሎች ህገ ወጥ የፈተና ተግባራትን ለማስቀረት ያስቻለ የአፈታተን ስርዓት ነው›› ብለውታል:: የሆነው ሆኖ፣ የፈተና ውጤቱ አስደንጋጭና አስገራሚ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም:: ከአጠቃላይ ተፈታኞች መካከል አራት በመቶ ያህሉ እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው ‹‹ሀገር ተረካቢ ነው›› ስለሚባለው ትውልድ በእጅጉ እንድንጨነቅ ያስገድደናል::

የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና አፈታተን ከዚህ ቀደም ከነበሩት የፈተና ስርዓቶች የተለየ እንደነበር ይታወሳል:: ተፈታኞች ፈተናውን የወሰዱት በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው ነበር፤ፈታኝ መምህራንም ፈተናውን እንዲፈትኑ የተደረገው መምህራኑ ያስተምሩባቸው ከነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ነበር::

ይህ የአፈታተን ስርዓት ኩረጃንና መሰል ህገ ወጥ የፈተና ተግባራትን ለማስቀረት እንደሚያግዝ ሲነገርም ነበር:: የፈተናው ውጤት ሲገለፅ የታየውን እውነት (ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ማነስን) ይዘን ‹‹ይህ ዓይነት ውጤት የተመዘገበው ኩረጃ ስላልነበር ነው›› የሚሉ ወገኖችን ሃሳብ ስናሰላስል፣ ‹‹ከዚህ ቀደም በነበሩት ዓመታት የተመዘገቡት ውጤቶች ካለፈው ዓመት የተሻሉ የሆኑት በኩረጃ ነበር ማለት ነው?›› ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን::

በሌላ በኩል የፈተናውን ውጤት በምን ዓይነት የትምህርት ስርዓት ውስጥ እያለፍን እንደምንገኝ በግልፅ አሳይቷል:: አራት ከመቶ ተፈታኞች እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው ትምህርትን እንዴት እየቀለድንበት እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው:: ይህ ደግሞ የሀገር ግንባታ ዋነኛ መሰረት የሆነው አምድና የሀገሪቱ ህልውና እጅግ አስደንጋጭ አደጋ ውስጥ እንደገባ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ለትምህርት ዘርፍ መሻሻልና የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት አዎንታዊ አስተዋፅዖዎችን እንዳበረከተ ባይካድም፣ ዓይነተ ብዙና ውስብስብ ችግሮችም አሉበት:: የትምህርትና ስልጠና ስርዓቱ በንድፈ ሀሳብ እንጂ የተግባር ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም። የምዘና ሥርዓቱም ለተግባራዊ እውቀት ትኩረት አልሰጠም። ስራ ፈላጊ እንጂ ስራ ፈጣሪ ትውልድ እየተፈጠረ አይደለም።

የምርምርና የቴክኖሎጂ ስራው ጎልብቶ ኢኮኖሚውን በሚፈልገው መጠን እያገዘም አይደለም። በዚህ ምክንያት ህብረተሰቡ በትምህርትና ስልጠና ሥርዓቱ የጥራትና የተገቢነት ጥያቄ እያነሳ ይገኛል። ከትምህርትና ስልጠናው እውቀት፣ ክህሎትና የስራ ፈጣሪነት አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ትውልዱ ዲግሪና ዲፕሎማ (ወረቀት) አምላኪ ሆኗል።

ኩረጃና መሰል ህገ ወጥ የትምህርትና ፈተና ተግባራት እየጎለበቱ በመምጣታቸው የትምህርት ስርዓቱ የሀገር ፍቅር፣ የብዝኃነት፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖርና ግብረገብነት እሴቶችን በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት በተጨባጭ ማስረፅ ባለመቻሉ ግለኝነት እያየለ፣ የጎሳ ብሄርተኝነት እየገነነ፣ የሀገር ፍቅር እየደበዘዘ መጥቷል። ይህም ሀገሪቱ የምትፈልገውን ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል::

የአንድ ሀገር የትምህርት ስርዓት መበላሸት የሀገሪቱ ህልውና አደጋ ውስጥ እንደገባ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል:: ሰላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ መረጋጋት ያለባት፣ ምጣኔ ሀብቷ ያደገና ፖለቲካዊ የሰከነ ሀገር እውን ማድረግ የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ስርዓት በተገነባ ትውልድ ነው:: ጥራት በሌለውና በወደቀ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ያለፈ ትውልድ ለሀገር ህልውና ትልቅ አደጋ ይሆናል::

በስነ ምግባር ያልታነፀና ኩረጃን መሳሪያ ያደረገ ተማሪ የሀገር ሸክምና አደጋ እንጂ የሀገርና የሕዝብ መኩሪያና መመኪያ ሊሆን አይችልም:: ለዚህም ነው ‹‹አንድን ሀገር ለማፍረስ ጦር ማዝመት ሳያስፈልግ፣ የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓት ማበላሸት በቂ ነው›› የሚባለውን ሃሳብ በተደጋጋሚ የምንሰማው::

በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ፣ ለሕግ ዘብ የቆሙ፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ ሆነው አጠቃላይ ሰብእናቸው የተገነባ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ስርዓት ነው።

አንዲት ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው:: የሰው ኃይል መገንቢያው ዋነኛው መሳሪያ ደግሞ ትምህርት ነው:: አስተማማኝና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ብቸኛው መንገድ ጥራት ያለው የትምህርት ስርዓትን መዘርጋት ነው::

ከቀናት በፊት ይፋ የተደረገው የ2014 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ውጤት፣ የትምህርት ስርዓቱን ክፍተቶች አሳይቷል:: ውጤቱ የትምህርት ስርዓቱ መውደቅ ለሀገሪቱ ህልውና ትልቅ አደጋ እንደሆነም አመላክቷል:: ስለሆነም ከዚህ ችግር ለመውጣት የሚያስችሉ የመፍትሄ አማራጮችን በፍጥነት መመልከትና መተግበር ያስፈልጋል::

የትምህርት ጥራትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ተማሪዎችን ያማከለ ዘመናዊና አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደት መከተል፤ የመምህራን ጥራትና ተነሳሽነት ማጎልበት፤ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን መከተል፤ ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ ጠንካራ የትምህርት ቤት አመራርን ማብቃት፤ ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፤ የማስተማሪያ ግብዓቶች ማሟላት እንዲሁም የተማሪዎች ስነ ምግባርን ማሳደግ ይገባል።

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚገባ የመከታተል፤ የመምህራን በጥራት የማስተማር፤ የትምህርት አመራር ስትራቴጂካዊ አመራር የመስጠት እንዲሁም የወላጆች ልጆቻቸውን በንቃት የመከታተልና የመደገፍ ተግባራት በቅንጅት ሊከናወኑ ይገባል።

በትምህርትና ስልጠና በቂ የሰው ኃይል ለማፍራት ባለፉት ዓመታት የትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የተሰሩ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት መገምገምም ይገባል::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ በሥነ ምግባር፣ በመልካም እሴትና በብቃት የታነጸ ዜጋን ለማፍራት በሚያስችል መንገድ የተቀረፀ፣ የሀገሪቱን ዕድገትና አንድነት በሚያስቀጥልና ለሀገር በቀል እውቀቶች ተገቢውን ትኩረት የሰጠ መሆኑን በሚገባ መፈተሽና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

# ነፃ ሃሳብ

# የትናንት ስህተቶቻችን የፈጠሩት የትምህርቱ ዘርፍ ስብራት

**ታምራት ተስፋዬ**

አንድ አገር ስኬትና ኪሳራን የምታወራርደው ባለመቻው፣ እልምታም ባበቃችው ትውልድ ነው። ትምህርት ደግሞ ይህን ትውልድ እውን ለማድረግና ለአንድ አገር እድገት መሰረት፣ ዋልታና ማገር ነው። የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅና የተደራሽነት መጠኑን ማስፋትም የአገርን እድገት አንድ እርምጃ ወደፊት ለማስቀጠል እጅግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም።

ኢትዮጵያ፣ ‹‹የበላና የተማረ ወድቆ አይወድቅም›› ፣ ተማር ልጄ... ተማር ልጄ.....ላልተማረ ሰው ቀኑ ጨለማ ነው››የሚለው የእናት አባት ምክር ከቃል አልፎ በሙዚቃ ተከሽኖ ትውልድ የተሻገረባት፣ ‹‹መማር ያስከብራል አገርን ያኮራል!››የሚለው ቃልም በዜማ ታጅቦ በዝማሬ ሲሰማ የቆየባት አገር ናት።

ትምህርትን በአግባቡ የተጠቀሙ እና ውጤታማ የትምህርት ሥርዓት የተከተሉ የዓለም አገራት ቁሳዊና ሰብዓዊ እድገታቸው ጎልቶ የሚታይ ነው::እንደ አገር ለቅኝ ገዢ የማትመቸው አገር ኢትዮጵያ፣ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓትን ከተዋወቀችበት ጊዜ ጀምሮ የትምህርት ስርዓቷን ነጻ ሳታደርገው ቆይታለች።ከዛም ሲሻገር ሥርዓተ ትምህርቷ ከውጪ አገራት ተጽዕኖ ብቻ ሳይሆን ከአገር ውስጥ ፖለቲካ ጫናም ጸድቶ ያውቃል ብሎ ደፍሮ መናገርም አይቻልም።

ኢትዮጵያም የምትከተለው ሥርዓተ ትምህርት ለድህነቷና በየዘመኑ ለሚነሳው አገራዊ ግጭት እንደ መንስኤ ተደርጎ ይወሰዳል።የአገሪቱ ዋና ችግር እንደሆነ የሚነገርለት የኢትዮጵያ ፖለቲካም የተበላሸው የትምህርት ሥርዓት ውጤት እንደሆነ ይነሳል።

የዘርፉ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ሲገልጹ እንደሚደመጡት ከሆነ፣ የኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ የቁልቁለት መንገዱ የፈጠነው የደርግን መንግሥት መውደቅ ተከትሎ ወደ ሥልጣን በመጣው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር(ኢሕአዴግ) የአገዛዝ ዘመን ነው::

በወቅቱ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች በስፋት የማድረስ ተልዕኮን እንደያዘ የሚያስበው ኢህአዴግ፤በማዳረስ ላይ የመተማመን ጉዞን በመራመድ የኢትዮጵያን የመማር ማስተማር ሂደት በማጥራት ሳይሆን በማብዛት በሽታ ሲገድለው ቆይቷል::

የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት በሚል በሚከናወኑ ተግባራት የትምህርት አቅርቦቱ ሊያድግ ይችላል:: ይሁን እንጂ ከዚህ ጎን ለጎን የጥራቱን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ መንገድ ካልተከተሉ ዞሮ ዞሮ አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆኖ መቅረት ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው::

የቀደሙት አመታት ለትምህርት ስርአቱ ሞት በተለይም ለጥራቱ ዝቅጠት ግንባር ቀደም መንስኤዎች ተብለው የተለዩ በርካታ ምክንያቶች ይዘረዘራሉ::የፈተና አሰጣጥ ሂደት ከዝግጅት እስከ ስርጭት ዝርክርክ መሆንም ከብዙ ችግሮች መካከል በቀዳሚነት ይነሳል::

እንደሚታወቀው ትምህርት የነገ የአገር ተስፋ የሆኑ ተማሪዎችን በእውቀት፣ አመለካከትና ሥነምግባር ቀርጾ የማውጣት ቁልፍ ሲሆን ፈተና ደግሞ የዕውቀት መለኪያ ነው። ፈተና ተማሪዎች በትምህርት ወቅት በገበዩአቸው እውቀቶች ልክ የሚፈተሹበትና የሚለኩበት ሚዛን ነው።

ይሁንና በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በፈተና አሰጣጥ ሂደት በሚስተዋሉ ድክመቶች ተማሪዎች በተደራጀ ሁኔታ ኩረጃ ላይ ሲተጉ ተስተውሏል። ኩረጃ በዕለት ተዕለት የትምህርት ስርዓት ወቅት የሚያጋጥም ቢሆንም በተለይ በብሔራዊ ፈተናዎች ላይ የሚከወንበት መንገድ ዘመን ባመጣው ቴክኖሎጂ የተደፈገ መሆኑ ኪሳራውን ከፍ አድርጎታል።

ኩረጃው በተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በፈተና ጣቢያ አስተባባሪዎች፣ በፈታኝ መምህራን፣ በመስተዳድር ኃላፊዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተለይም ስማቸውን በመሸጥ ጥሩ ገቢ ለማግኘት በሚጥሩ ትምህርት ቤቶችም ጭምር መቀነባበሩም የኢትዮጵያን የትምህርት ስርአት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎት ቆይቷል።በመንግስት በኩል ችግሩን ለመከላከል ለተከታታይ ዓመታት የተለያዩ ተግባራት ቢከናወኑም ውጤታማ መሆን ግን አልተቻለም።

**በሺህ የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ እንኳን ለማሳለፍ ያልቻሉበት ሁኔታና የተማሪዎቹ መውደቅ በትምህርት ስርዓቱ ለረዥም ጊዜ ሲጠራቀሙ የመጡ ብልሹ አሠራሮች ውጤት ነው**

ለአገሪቱ ትምህርቱ ጥራት ውድቀት እንደ ምክንያት ከሚነሱ ችግሮች መካከል ሌላኛው ተማሪዎችን ያለማውደቅ ዘይቤ (Zero Attrition Rate) የሚለው የተሳሳተ ሐሳብ በዋነኝነት ይነሳል::ይህ እሳቤ ተማሪዎች ‹‹ባናጠናም እናልፋለን›› በሚል አስተሳሰብ እንዲያድርባቸውና ሳይዘጋጁ ለፈተና መቅረብ የተለመደ እንዲሆን አድርጎት ቆይታል::

ከአገሪቱ ካስቀመጠችው አነስተኛ ማለፊያ ነጥብ እጅግ ያነሰ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉት የትምህርት እርከኖች ቁጥራቸው እየበዛ መምጣቱ ሳያንስ፤ ወደ መሰናዶ ትምህርት የገቡት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት አሳፋሪ ሁኔታ ፈጥሯል።

ምንም እንካን በርከት ያሉ ዩኒቨርስቲዎች ተገንብተው አገልግሎት መስጠታቸው እሰይ የሚያስብል ቢሆንም ቀደም ባሉት አመታት አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የሚከፈቱት ለብዙሃኑ እንደሚታደል መሰረታዊ ሸቀጥ ተቆጥረው መሆኑም ሌላው ለዘርፉ ራስ ምታት እንደነበር ይታወሳል::የዩኒቨርሲቲዎቹን አቅምና ፍላጎት ከመዳሰስ ይልቅ ተማሪዎችን በገፍ ለማስመረቅና ለፖለቲካ ጥቅም እንጂ፣ለአካባቢው ሕዝብ ብሎም ለአገሪቱ ዕድገት በሚያስፈልግ መልኩ ተገቢው ጥናት ተደርጎባቸው አልነበረም::

በእነዚህና በሌሎችም ግዙፍ ችግሮች በአጠቃላይ በትምህርት ተግተው እውቀት ሸምተው ኢትዮጵያን ለመጥቀም የሚታትሩና ለትምህርት ትኩረት በመስጠት የሕይወት መስመራቸውን የሚያስተካክሉ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ እንዲሽቆለቆል አድርጎታል።

የትምህርት ሥርዓቱ በመሰል ሰንሰለቶች ተተብትቦ መስመር ሊይዝ ባለመቻሉ እና ተቆርቋሪ ባለቤት በማጣቱም አገሪቱ የተማረና የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል እያጣች፣ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችም በየጊዜው ሲባባሱ አስተውለናል::

ትምህርት በኢትዮጵያ እጅግ ውስብስብ ለሆኑ የፖለቲካ ቀውሶች መነሻ ሲሆን የታየበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: ዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ በየጊዜው የሚያገረሸው የብሔር ፖለቲካ ውዝግብና የተማሪዎች ግጭት ከጥናትና ምርምር ይልቅ ዩኒቨርሲቲዎችን ዝነኛ ሲያደርግ ይታያል::ብሔራዊ ፈተናዎች ጊዜያቸው በደረሰ ወይም ውጤት በተለጠፈ ቁጥር፣ በአገሪቱ የሚነሳው የፖለቲካ ውዝግብ ደግሞ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ሲሄድ ታዝበናል::

በመሰል መፍትሄ በራቃቸው ችግሮች ከአመት አመት ‹‹ያልተማሩ አባቶቻችን ያቆዩዋትን አገር የተማሩ መኃይማን ደርሰው አፈረሷት›› ሲባል መስማት የተለመደ እየሆነ መምጣቱን ተከትሎም፣የዘርፉ ምሁራንም ሳይውል ሳያድር ጊዜና አቅም ሰጥቶ የትምህርት ሥርዓቱን ማሻሻል እስካልተቻለ ድረስ አገሪቱ አስከፊ ቀውስ ውስጥ ትገባለች በሚል በተደጋጋሚ ሲወተውቱም ቆይተዋል::

ይህ ውትወታ ታዲያ በተለይ ከኢሕአዴግ ከሥልጣን መወገድ በኋላ፣ ሰሚ ጆሮ ማግኘት የቻለ ሲሆን የለውጡ መንግስትም እንደ መፅሃፍ ቅዱስ ቃል ሳይነካ የቆየውንና የአገሪቱን ትምህርት እንዘጭ እንቦጭ ሲያደርግ የከረመውን ፖሊሲ ለመለወጥ ትኩረት ሰጥቷል::

ቀድሞ የነበረውን የትምህርት ዘርፍ ችግር ያስቀራል የተባለ የትምህርት ማሻሻያም ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ሲደረግ የቆየ ሲሆን፤ በዚህም የትምህርትና የሥልጠና ፍኖተ ካርታ ከማዘጋጀት ጀምሮ አዳዲስ አሠራሮችን አስተዋውቃል::

አዲሱ ፍኖተ ካርታው ሙያው ላይ ባሉ ምሁራን የተዘጋጀ፣ ለበርካታ ዓመታት የተደረገን ጥናት መሠረት ያደረገ እንደመሆኑም ለግብረ ገብነት፣ለአገር በቀል ዕውቀት፣ለሙያና የቀለም ትምህርት፣ ለቴክኖሎጂ፣ ምርትና ተግባራዊ፣ ጥናትና ምርምር ትኩረት ተሰጥቷል::

በአዲስ ስርአት ትምህርት ቀደም ሲል ይስተዋሉ የነበሩና ዘርፉን ተብትበው ያሰሩ ሰንሰለቶችን ለመበጣጠስ ይረዳሉ በሚል ከተለዩ መፍትሄዎች መካከልም የፈተና ስርአቱን ፈር ማስያዝ ዋነኛ ሆኖ ይጠቀሳል::በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተማሪዎች ዘንድ እየተስፋፋ የመጣውን ኩረጃና የፈተና ስርቆት ለመግታት በተለይ ባለፈው ዓመት ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ሰፊ ቅድመ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል።

በተለይ ኩረጃና የፈተና ስርቆት ለመከላከል፣ ኩረጃን የሚጸየፍ ትውልድ ለመፍጠርና በማህበራዊ ሚዲያው ከዕውቀት ይልቅ ጥፋትን ለሚዘሩ የጥፋት መልዕክተኞች እድል ላለመስጠት ዘንድሮ በፈተና አሰጣጥ ሂደት ላይ ስር ነቀር ለውጥ አድርጓል።ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋማት ብሄራዊ ፈተናው እንዲሰጥ ተደርጓል።

የብሔራዊ ፈተና ተፈታኞችን በየዩኒቨርሲቲው በመውሰድ ለኩረጃ ፍፁም አመቺ በማይሆን መንገድ እንዲፈተኑ የማድረጉ ዕርምጃ፣ ትምህርት ሚኒስቴርን ለብዙ ትችቶች ያጋለጠ ደፋር ዕርምጃ እንደነበር የሚታወስ ነው::ይሁንና በትግበራው ሂደት ከሌሎችም ነባራዊ ሃቆች ጋር ተዳምሮ የሚፈለገው ምት መምታት ችሎ አሳይቷል::ዘንድሮ የ2014 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ከወሰዱት 996 ሺህ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ያለፉት 3 ነጥብ 3 ከመቶ ወይም 29 ሺህ 909 ብቻ መሆናቸው ለዚህ ምስክር ሆኖ መቅረብ የሚችል ነው::

እንደ እኔ እምነት በዘንድሮ የ12ኛ ክፍል የብሔራዊ ፈተና አሰጣጥና ዕርማት ሒደትን ትምህርት ሚኒስቴር በጥብቅ ሒደት እንዲካሄድ በማድረጉ በመጨረሻ የመጣው ውጤት የኢትዮጵያ ትምህርት የሚገኝበትን የጥራት ጉድለት ያለንበትን ቀውስ ብሎም የችግሩን ልክ በአግባቡ፣ በአሐዝ መረጃ ፍንትው አድርጎ አደባባይ አውጥቷል::

በሺህ የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች አንድ ተማሪ እንኳን ለማሳለፍ ያልቻሉበት ሁኔታና የተማሪዎቹ መውደቅ በትምህርት ስርዓቱ ለረዥም ጊዜ ሲጠራቀሙ የመጡ ብልሹ አሠራሮች ውጤት ነው:: የተማሪዎቹ አስከፊ ውድቀት የቀድሞው ስርአተ ትምህርት ድምር ውጤት ነው::

ከተፈታኞቹ ሃምሳ ከመቶና ከዚያ በላይ ጥያቄዎቹን መልሰው ለማለፍ የቻሉት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ አናሳ መሆን ቀደም ባሉት አመታት ይሰጥ በነበረው ፈተና በአብዛኛው ተማሪዎቹ ውጤት እንጂ እውቀት እንደሌላቸው ፍንትው አድርጎ ያስመለከተ ነው::

የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት ዛሬ የተፈተኑትን ተማሪዎች የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ከተመለመሉበት፣ ከሠለጠኑበት መንገድ፣ አጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ከተመራበት ፖሊሲና አቅጣጫ እና ከሌሎች ብዙ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ፤ ባለፉት አሥርት አመታት የሄድንበት የተንሻፈፈ ጉዞ ውጤት ነው።

ይህን ከመረዳት ይልቅ ከዚህ በተቃራኒ መንግሥት በትምህርት ጥራት ማስጠበቅ ስም የብዙ ተማሪዎችን የወደፊት ሕይወት በፈተና እያበላሸ ነው የሚል ትችት የሚሠጡ ይሰማሉ::ይሁንና መራርም ቢሆን ሃቁን ልንቀበልና እየመረረንም ልናጣጥመው ይገባል::

የመንግስት የለውጥ ጉዞ እርምጃውም ኢትዮጵያ በቂ የተማረ እና ለውጥ የሚያመጣ ትውልድን እንድታገኝ ትልቅ አቅም የሚሰጥ ነው:: መሰል አሰራር በስርቆት መተማመንም ሙሉ በሙሉ ያስቀራል:: ከስርቆት ይልቅ በራሱ አቅም የሚተማመንና በእውቀት የላቀ ትውልድን ለመፍጠር አቅም ይፈጥራል::

በእርግጥ ከብዙ ጥናትና ሙግት በኋላ ኩረጃና ሥርቆትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ተግባራዊ የተደረገው የተማከለ የፈተና ስልት ያስገኘው ውጤት ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ መደናገጥን ሲፈጥር ታይቷል።ለረዥም ዘመን ሳይገለጥ፣ አልፎ ተርፎም እንደ ትክክለኛ ነገር ሲቆጠር የኖረን ማኅበራዊ ስብራት በሆነ አጋጣሚ ተገልጦ ፊት ለፊት ሲጋፈጡት በመጀመሪያ በድንጋጤ ተውጦ የሚያደርጉት ቢጠፋ እምብዛም አይደንቅም፤ ተፈጥሯዊ ምላሽም ነው።

ይሁንና ጉዳዩንና የነገሩን መሠረት ለመካድ መሞከር ወይም ሰንካላ ሰበብ እያስቀመጡ ማለፍ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ አያመጣም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉትም፣ለወባ በሽታ የወባ መድኃኒት እንጂ፣ ገና ለገና በሽታው እንደ ራስ ምታትና ብርድ ብርድ የማለት ምልክቶችን አሳየ ተብሎ የብርድና የራስ ምታት ማስታገሻ መድኃኒቶችን እንደ ዘላቂ መፍትሔ አይወሰድም። ችግሮች ሲገጥሙ ጣት መጠቆምና በቀዳዳ ሾልኮ ማምለጥ የሞኞችና የፈሪዎች መፍትሔ ሲሆን፤ ትክክለኛው የብልህና የጀግኖች መንገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ፊት ለፊት ተጋፍጦ በጥበብ ለመርታት መፍጨርጨር ነው።

ችግሩ በአንድ ሌሊት እንዳልተፈጠረ ሁሉ መፍትሔውም በአንድ አዳር ሊመጣ አይችልም። ዛሬ ከአበባ አልፎ ፍሬውን ያየነውን የትምህርት ችግር ቀልብሶ ለማስተካከል ረጅም ጊዜና ከባድ ዋጋ ይጠይቃል። የትናንት ስህተታችን የፈጠረውን የዛሬ ስብራታችንን ተረድተን ዘላቂ መፍትሔ ከሚፈጥሩት ወገን ለመሆን መዘጋጀት አለብን። አዲስ ሃሳብና ጉልበት ለመገስገስ ተስፋ ሰንቀን እንነሳ፤ ለላቀ ለውጥና ለተሻለ ነገ እንትጋ። እንደ ሀገርና እንደ ማኅበረሰብ የሚያዋጣን መንገድ ይሄ ነው።

ታዋቂው የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን እንዳለውም አንድን ነገር በተመሳሳይ ዘዴ ደግሞ ደጋግሞ በመስራት የተለየ ውጤት መጠበቅ እብደት ነው::በመሆኑም አዲሱን የለውጥ መንገድ የግድ ልንቀበልና በተለየ መንገድ በመራመድ ለችግሩ መፍትሄ ልንሰጠው ይገባል::መንግስት የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ መርምሮ አሳሪና ለትምህርት ጥራት መውደቅ ምክንያት የሆኑ ስንክሳሮችን ማውጣትና መሰል ደፋርና ውጤታማ ተጨባጭ ስራ መስራቱን ሊቀጥል ይገባል::

በመጨረሻም አንድ ነገር ብዬ ላብቃ:: አሁን ባለው ሁኔታ ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችል ትኬት የቆረጡት 30 ሺ የሚሆኑት ብቻ ናቸው::ይሁንና መንግስት የዘንድሮን የዩኒቨርሲቲ የመቀበል አቅም ታሳቢ ባደረገ እና ትግበራው በአገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ እንደመሆኑ ለአንድ ጊዜ በሚከወን መልኩ ለአንዳንድ ተማሪዎች እድል መስጠትን ታሳቢ ማድረግ ቢችል መልካም ነው::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ‹‹ እንደ አገር አሸናፊ እንድንሆንና ቀድመን መገዝ እንድንችል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን››

### የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያው አቶ መርዕድ በቀለ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አሁን ባለንበት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን ከዘመኑ ጋር እየዘመነ መሄድ ይጠበቅበታል። እየዘመነ የመጣውን ቴክኖሎጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ስለመሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎችም ያስገነዝባሉ። ለእዚህ ደግሞ ቴክኖሎጂውን ተደራሽ ማድረግ ላይ በትኩረት መሰራት ይኖርበታል፤ ተደራሽነቱ ደግሞ በመሰረተ ልማት ብቻ አይደለም፤ መሰረተ ልማቱ የሚፈልጋቸውን ቴክኖሎጂዎች ቁሳቁስ ማቅረብ፣ ባለሙያዎችን ማሰልጠን ወሳኝ ጉዳይ ናቸው፡፡

ይህ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለስራ፣ ለኑሮና ለመሳሰሉት አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በጥንቃቄ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል። ሰዎች መረጃዎችን በፍጥነትና በጥራት የሚለዋወጡበት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተለይም የኢንተርኔት ተደራሽነት እያደገና እየሰፋ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አገልግሎት በሚውልበት ወቅት ጥንቃቄ ማድረግም ይገባል።

በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችንም እጅግ ከፍተኛ አቅም ያለውና በእያንዳንዱ የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ እያበረከተ የሚገኘው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፋይዳ፣ ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት መከተል ስለሚገባ ጥንቃቄ ኢትዮጵያ በዘርፉ ስላለችበት ደረጃ ከዘርፉ ባለሙያ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ይዘን ቀርበናል። ባለሙያው የአይ ኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መርዕድ በቀለ ናቸው።

አቶ መርዕድ በቀለ የአይ ኢ ኔትዎርክ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። በቴክኖሎጂው ዘርፍ ተሰማርተው ወደ ሥራ ከገቡ 14 ዓመታትን አስቆጥረዋል። ባንኮችን ጨምሮ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ለዩኒቨርሲቲዎችና ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ትላልቅ የዳታ ማዕከላትን ከመገንባት ጀምሮ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅትን አቋቁመው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በአሁን ወቅትም በድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ያለውን የዳታ ሴንተር በማሳደግና በማስፋፋት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ለመስጠት ስምምነት በማድረግ ወደ ሥራ ገብተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በዚህ ዘመን ለአንድ ሀገር ያለው ፋይዳ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ መርዕድ፡-** በአሁኑ ዘመን ሰዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃዎችን በፍጥነትና በጥራት የሚለዋወጡበት አንዱ መንገድ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው። በተለይም የኢንተርኔት ተደራሽነት እያደገና እየሰፋ የመጣ ሲሆን፣ ዓለምን ሙሉ ለሙሉ አንድ በማድረግ ሰዎች ከዚህኛው ጫፍ እስከ ወዲያኛው ጫፍ በቀላሉ እንዲገናኙና መረጃ እንዲለዋወጡ የሚደርግበት ቀልጣፋ አገልግሎት ነው፡፡

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። በተለያየ ዘርፍ አስገብተን ብንጠቀመው አበርክቶው የጎላ ነው። ለአብነትም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ለትምህርት ከሚሰጠው አበርክቶ አንጻር ብንመለከተው ትምህርት ላይ አስፈላጊ የሆኑ በርካታ መረጃዎችን ማግኘት ያስችላል። ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ትምህርትን በዘመናዊ መንገድ፣ በርቀትና በጥራት ለመስጠት ይጠቅማል።

በጤና ዘርፍም አገልግሎት መስጠት ይቻላል። በተለይም የጤና ባለሙያ እጥረት ባለበት አገር ውስጥ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ አቅም ያላቸውና ጥቂት ቁጥር ያላቸው የጤና ባለሙያዎች ቴክኖሎጂን በመጠቀም በርካታ ቁጥር ያላቸው ታካሚዎች ዘንድ መድረስ ይችላሉ። የመንግሥት አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመስጠት ቴክኖሎጂ ወሳኝ ነው። ከታችኛው መዋቅር ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የመንግሥት መዋቅር ድረስ ቴክኖሎጂን መጠቀም ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡

ቀበሌ ላይ ፋይል ጠፋ ሲባል ይሰማል። ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም ከተቻለ በቀላሉ ፋይሉን መለየት ይቻላል። ውሃ፣ መብራትና ሌሎችንም ክፍያዎች ለመክፈል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በትልቁ ያግዛል። የግብርና መረጃዎችንም እንዲሁ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ያግዛል። ስለዚህ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማንኛውም የሰው ልጆች የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ የተቀላጠፈ አገልግሎትን በፍጥነትና በጥራት ተደራሽ የማድረግ ትልቅ አቅም አለው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በየትኛው ዘርፍ መጠቀም ቢቻል ይበልጥ ውጤታማ መሆን ይቻላል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ መርዕድ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ የተሻለ ነው። ምክንያቱም የሁሉም ነገር መሰረት ትምህርት ነውና ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም ያስፈልጋል። ጥራት ያላቸው ትምህርቶች ተቀርጸው በርቀት መስጠት ቢቻል የተሻለ ነው።

በአሁኑ ወቅት የውጭ አገር ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ ለሙሉ ትምህርት የሚሰጡት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ነው። ተማሪው በፈለገውና ባመቸው ሰዓት እየፈለገ የሚጠቀምባቸውና መማር የሚቻልባቸው ቴክኖሎጂዎች ተሰርተዋል። በእኛ አገርም ይህንኑ ማዕከል በማድረግ ቢሰራ መልካም ነው። በአሁኑ ወቅት የስልክ አገልግሎት ብዙ ቦታ እየደረሰ ነው። ኢንተርኔት በየቦታው ተደራሽ እየሆነ ይገኛል።

ስለዚህ ገጠር ውስጥ ርቆ ያለውም ተማሪም ይሁን ከተማ ውስጥ ያለው ተማሪ ተመሳሳይና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ላይ መሥራት ያስፈልጋል። ተማሪው ጥራት ያለው ትምህርት ይዞ ሲወጣ፤ ኢኮኖሚውን መቀየር ይችላል። የመንግሥት ኃላፊውም፣ የባንክ ሠራተኛውም፣ የጤና ባለሙያውም፣ ነጋዴ የሚሆነውም ሁሉም ከትምህርት ይዞት በሚወጣው ልክ ነው ሊሰራ የሚችለው። ስለዚህ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጀመሪያ ለትምህርት በሚገባ መጠቀም ቢቻል እጅግ በጣም ጥሩና የሚያመጣው ውጤትም ትልቅ ነው፡፡

ሁለተኛው የመንግሥት አገልግሎቶችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፉ ማድረግ ያስፈልጋል። ብዙ ሰዎች በመንግሥት አገልግሎት ሲማረሩ ይሰማል። ለችግሩ የተለያየ ምክንያት ቢኖረውም ቴክኖሎጂ ብንጠቀምና መረጃዎች በሲስተም ተደራጅተው መቀመጥ እንዲችሉ ቢደረግ መረጃ ጠፋ አይባል፤ የመረጃ መፋለስ አያጋጥምም ባጠቃላይ ከቅሬታ የጸዳ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይቻላል። ለዚህም ሠራተኞችን በትንሽ ስልጠና ማብቃት ይቻላል፡፡

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በአሁኑ ወቅት ከመንግሥት ተቋማት ይልቅ የግል ዘርፎች በበለጠ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። ለአብነትም ባንኮችን መጥቀስ ይቻላል። ባንኮች ያለ ኮር ባንኪንግ አይሰሩም። በዚህም አንድ ቅርንጫፍ ላይ አካውንት የከፈተ ሰው ሌላ ቦታ ሄዶ ገንዘቡን ማውጣት ይችላል። በኤቲኤም ማሽን ገንዘብ ማውጣት ይቻላል። በሌሎችም ዘርፎች ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተግባራዊ እየሆነ ነው። ነገር ግን የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ትምህርት ላይ በስፋት ማየት አልተቻለም። ይህም ወደኋላ አስቀርቶናል፡፡

ግብርና ላይ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በደንብ መጠቀም ይቻላል። እንደሚታወቀው በአገሪቱ ያለው መሬት የአገሪቷን ህዝብ አጥግቦ ለውጭ ኤክስፖርት ማድረግ የሚያስችል አቅም አለው። ይሁንና አገሪቷ በተፈጥሮ የተሰጣትን ይህን ጸጋ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለመጠቀም አልሰራንበትም። ቴክኖሎጂን ብንጠቀም የት ቦታ ላይ ምን የተሻለ ምርት ማምጣት ይቻላል? በየአካባቢው ምን አይነት በሽታዎች አሉ? የአየር ሁኔታው ምን አይነት ነው? የትኛው ቦታ ላይ ነው ምርጥ ዘር መጠቀም ያለብን እና ሌሎች ጥያቄዎችንም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም መመለስ ይቻላል። በስፋት ለሚያመርተውም ሆነ በትንሽ መሬት ላይ ለሚያመርተው አርሶ አደር መረጃው ጠቃሚ ነው። ስለዚህ እንደ አገር ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ትምህርት፣ የመንግሥት አገልግሎትና ግብርና ላይ በደንብ ብንጠቀምበት ውጤታማ በመሆን አገርን መቀየር እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- በእርስዎ ምልከታ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ኢትዮጵያ በምን ደረጃ ላይ ናት ማለት ይቻላል? ችግሮቹና መፍትሔውስ?**

**አቶ መርዕድ፡-** እውነት ለመናገር በጣም በብዙ ወደኋላ ቀርተናል። እርግጥ ነው ዘግይተን በመምጣታችን ያገኘናቸው ጥቅሞችም አሉ። ለአብነትም ስልክን ብንመለከት እንደሌሎች አገራት ከአናዶል ስልክ ተነስተው ከዛም ዲጅታል ስልክ፣ ፋክስና ሌሎችንም በሂደት ተጠቅመው ቀስ በቀስ ነው አሁን ላይ የደረሱት። እኛ ግን ዘግይተን ወደ ቴክኖሎጂው በመምጣታችን በአንድ ጊዜ ሁሉንም አልፈን አሁን የተደረሰበትን ቴክኖሎጂ ዛሬ ገዝተን ማምጣትና መጠቀም ችለናል። ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የማምጣት ዕድሉም አለን።

ቴክኖሎጂን በይበልጥ እየተጠቀምንበት ያለው ግን ለማህበራዊ ሚዲያ ለፌስቡክ እና ለዩቲዩብ ነው። ብዙ ሰዎች ዩቲዩብ ላይ ነው ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ፤ ዳታዎች ቢታዩ የሚያሳዩት ይህንኑ ነው። ከዛ ይልቅ ግን ሰዎች ኑሯቸውን ለማሻሻል፣ ትምህርትን ለማሻሻል፣ የመንግሥት አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ግብርናን ለማሻሻል እና ሌሎች ኑሯችንን ቀለል ማድረግ ለሚያስችሉ ተግባራት ብናውለው በአጭር ጊዜ ብዙ ነገሮችን መለወጥ እንችላለን።

በሌላው ዓለም ቴክኖሎጂን በመጠቀም በቤታቸው ተቀምጠው ሁሉንም ነገር ያገኛሉ። እኛ ግን ወደኋላ በመቅረታችንና በሚፈለገው መንገድና ልክ ቴክኖሎጂን ባለመጠቀማችን ምክንያት ዛሬም ለመብራት፣ ለውሃና ለሌሎች ክፍያዎች እንሰለፋለን። በዚህም ጊዜና ጉልበት እናባክናለን። ስለዚህ ቴክኖሎጂን በአግባቡ ጥቅም ላይ ልናውለው ይገባል።

እርግጥ ነው በትራንስፖርት ላይ እየታየ ያለ ለውጥ አለ። እሱ ጥሩ ነው ራይድ፣ ፈረስና ሌሎችም ቴክኖሎጂን በመጠቀማቸው ይህን አገልግሎት ማግኘት ችለናል። ነገር ግን ከዚህ በበለጠ የዕለት ተዕለት ኑሯችንን ማቅለል የምንችልባቸው ብዙ አይነት ቴክኖሎጂዎች ያሉ ቢሆንም የአብዛኛው ሰው ትኩረት በማህበራዊ ሚዲያው ላይ በመሆኑ ገና ብዙ ይቀረናል። አልተጠቀምንበትም።

ለዚህም አንደኛው ማነቆ በአገሪቱ የነበረው አንድ ቴሌኮም ብቻ የነበረ በመሆኑና የአገልግሎት አሰጣጡ ጥሩ ስላልነበረ ነው። አሁን ግን ተጨማሪ ቴሌኮም መጥቷል። ነባሩም አገልግሎቱን በደንብ እያሻሻለ ነው። በዚህም የቴክኖሎጂ ተደራሽነት እየጨመረ መጥቷል። ሁሉም ሰው የኢንተርኔት ተደራሽ መሆን ችሏል። ነገር ግን ይህን ተደራሽነት ለፌስቡክና ለዩቲዩብ ብቻ መጠቀም ሳይሆን ልክ እንደፈረስና ራይድ ሁሉ ለውሃ፣ ለስልክ፣ ለግብር መክፈያና ለሌሎች አገልግሎቶችም መጠቀም ቢቻል ብዙ ለውጦችን ማምጣት ይቻላል። አንደኛ ሰውዬው ታክስ ለመክፈል ጊዜውን አያባክንም። ሁለተኛ መንግሥትም ተገቢውን ክፍያ በጊዜው መሰብሰብ ይችላል። ስለዚህ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር ለዘርፉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷል ብለው ያምናሉ ካልሆነስ ለምን?**

**አቶ መርዕድ፡-** በሃሳብ ደረጃ ቴክኖሎጂ ላይ መሥራት እንዳለብንና ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ይታመናል። በተግባር ግን ለዘርፉ በቂ ትኩረት ተሰጥቶታል ብዬ አላምንም። ዘርፉ መበረታታት አለበት። ቴክኖሎጂው እንዲያድግ አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል። በዘርፉ ውስጥ ያሉት ኩባንያዎችም በራሳቸው ጥረት ነው እየተጓዙ ያሉት እንጂ ዘርፉን የሚደግፍና ግልጽ የሆነ ፖሊሲ የለም።

ለዚህም አንዱ እንቅፋት የሆነው ፍራቻ ነው። ምክንያቱም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከፍተኛ አቅም ያለው ነው። ዓለም በቴክኖሎጂ ብዙ ርቀት የተጓዘ በመሆኑ ሳይበር አታክ ቢያጋጥም ሙሉ ከተማን በአንድ ጊዜ መብራት ማጥፋት ይቻላል። ለምን ሙሉ ከተማው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተገናኝቷል። የሆነ አገር ላይ የተቀመጠ አንድ አጥፊ ሙሉ ከተማዋ ውሃ እንዳታገኝ ማድረግ ይችላል። ባንክ ላይ ያሉ ገንዘቦችን በአንድ ጊዜ ጠራርጎ ሊወስድ ይችላል። የዚህን ያህል አቅም አለው።

ስለዚህ ቴክኖሎጂ ጥቅም እንዳለው ሁሉ የሚያስከትለው አደጋም በዚህ ልክ ከፍተኛ በመሆኑ ጥንቃቄ ያሻዋል። ቀዳዳዎች በሙሉ በአግባቡ መዘጋት አለባቸው። ለዚህም ሳይበር ሴኪዩሪቲ የሚባለው ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በመንግሥት ደረጃ የተቋቋመው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነትም (ኢንሳ) ዋና ሥራው ይህ ነው። እናም የሳይበር ደህንነት ልክ መከላከያ ብለን አገርን እንደምንጠብቀው ሁሉ ሳይበር የሚባለውንም መጠበቅ ካልቻልን ይዞት የሚመጣው አደጋ ከፍተኛ ነው። ይህ ሥራ መሠራት አለበት። ነገር ግን ‹‹ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደረም›› እንደሚባለው የሚመጣውን አደጋ በመፍራት ኋላቀር ሆነን ልንቀር አንችልም። ስለዚህ ቴክኖሎጂውን እያለማን ጎን ለጎን ደግሞ ቴክኖሎጂው ሌላ አደጋ ይዞ እንዳይመጣ መጠንቀቅና መጠበቅ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ**

**አቶ መርዕድ፡-** ያለንበት ዘመን ያለጥርጥር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ነው። ዓለም እየተንቀሳቀሰች ያለችው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው። ሌላው ቢቀር ያለ ኢንተርኔት ሥራ መሥራት አይቻልም። ወደፊት ደግሞ የባሰ ቴክኖሎጂ አስገዳጅ እየሆነ የሚመጣበት ጊዜ ነው። ስለዚህ እንደ አገር አሸናፊ እንድንሆንና ቀድመን መጓዝ እንድንችል ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን። ለቴክኖሎጂ ትኩረት ከሰጠን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሌሎች ዘርፎችን ማለትም ግብርናን፣ ጤናንን፣ ትምህርትን፣ የባንክ ሥራን፣ ነጋዴውና መንግሥትንም ጭምር እናግዛለን። በተለይም አገር በቀል የሆኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች እንዲበረታቱና በየዘርፉ ገብተው ማገዝ እንዲችሉ መደገፍ ያስፈልጋል። ቴክኖሎጂ እያደገ ሲመጣ የውጭ ባለሃብቶችን በቀላሉ መሳብና ኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስላደረጉልን ትብብር እናመሰግናለን!**

**አቶ መርዕድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ!



# ወቅታዊ ትንታኔ

# ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ስለኢትዮጵያ አሉታዊ መንገድን ለምን መረጡ?

**ክብረአብ በላቸው**

ሲኤንኤን እና ቢቢሲ ሌሎችም ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ኢትዮጵያን በተመለከተ በሚያስተላልፉት ዘገባ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ይደመጣሉ:: በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ላይ ኢትዮጵያ የምትቀርብበት ጊዜን እና መንገድ እንዲሁም የአቀራረባቸው ሁኔታን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የሚሉት አላቸው::

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን መምህር እና ተመራማሪ ዶክተር ደምመላሽ መንግስቱ እንደሚናገሩት፤ በዋናነት ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃኑ ቅድሚያ የሚሰጡት ለራሳቸው እና ያሉበት ሀገር መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ሀገራት ነው:: በዋናነት ለራሳቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ:: የአሜሪካ ሚዲያ ቅድሚያ ለአሜሪካውያን ይሰጣል:: ከሀገሮቹ ፍላጎት አንፃር የእንግሊዙ ቢቢሲ ከእንግሊዝ ውጭ ላሉት ሀገሮች የሚሰጠው ትኩረት አንድ ዓይነት አይደለም::

ዓለም አቀፍ ተብለው እንደሞዴል የሚታዩ መገናኛ ብዙኃን በጥቅስ ምልክት ውስጥ የሚገቡ ናቸው:: ምክንያቱም የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ የሚያዩበት ሁኔታ፣ ስነምግባራቸው በጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ እና የተዛባ በመሆኑ ነው:: እነቢቢሲ፣ ሲኤን ኤን እና አልጀዚራ የሚባሉት ትላልቅ መገናኛ ብዙኃን በሙሉ ስለተለያዩ ሀገሮች በተለይ ደግሞ ስለአደጉ ሀገሮች እና እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ድሃ እና ያላደጉ ሀገሮችን በተመለከተ የሚዘግቡበት መንገድ እና የሀገራቱን ሁኔታ የሚረዱበት እንዲሁም ለዓለም የሚያስረዱበት ሁኔታ የተሳሳተ እና ደሃ ነው::

ዶክተር ደምመላሽ ፤‹‹መገናኛ ብዙኃኑ የአዘጋገባቸው ሁኔታ ድሃ ነው›› ለማለት ያነሳሳቸው፤ እውነታውን ከማሳየት ይልቅ በራሳቸው መነፅር እንዲሆኑ የሚፈልጉትን ያላደጉ አገሮች ተገዢነትን ሲያንፀባረቁ ይታያል:: እይታቸው የተንሸዋረረ ነው:: እነርሱ የሚፈልጉት ሲከሰት ማለትም ሀገሮች ላይ ቀውስ ሲፈጠር በተደጋጋሚ ይዘግባሉ::

ያደጉ እና ሃያላን ሀገራት ባላደጉት ሀገሮች ላይ የተለያዩ ሴራዎችን ሲሸርቡ፤ የጠሉትን መሪ ለማውረድ ሲሉ ያላደጉ ሀገሮችን መሪዎች ስማቸውን ይጠፋል:: ደካማ ጎን በመፈለግ ያራግባሉ:: ሀገሮቹን ለብጥብጥ እና ለቀውስ ይዳርጓቸዋል፤ በመጨረሻም መንግስታትን የሚለወጡባቸው ሁኔታዎች ይፈጠራል:: ይህ ሲሆን ዓለም አቀፉ መገናኛ ብዙኃን በተደጋጋሚ ይዘግባል:: ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፤ በማለት ኢትዮጵያን በተመለከተም የሚዘግቡበትን መንገድ ያብራራሉ::

ወደ ኢትዮጵያ ጉዳይ ሲመጣ በተመሳሳይ መልኩ አንድ የጥይት ተኩስ ድምፅ ተሰማ ሲባል፤ በተደጋጋሚ እያራገቡ ይዘግባሉ:: ከዛ ውጭ ስኬቶችን፣ ለውጦችን፣ የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ እና ልማትን በተመለከተ በምንም መልኩ በዘገባቸው አይሸፈንም:: በሚያስገርም መልኩ ስንዴ ቢመረት ዘርፈ ብዙ ለውጦች ቢታዩም በጣም የተዛባ እና የተንሸዋረረ እይታ ስላላቸው መልካሙን ውጤት አያሳዩም።

ዶክተር ደምመላሽ እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ጥቁሮች ከነጮች እኩል መሆናቸውን ከጥንት ጀምሮ ለዓለም ያሳየች ብቸኛዋ ታሪካዊ ሀገር ነች:: ይሄ ለእነርሱ ታሪካዊ የፖለቲካ ጠባሳቸው ነው:: በሌላ በኩል ኢትዮጵያን እንደፈለጉ ለማድረግ ሲሞክሩ እምቢ የሚላቸው ሲመጣ ኢትዮጵያ ላይ ዘመቻ እንዲካሄድ ያደርጋሉ:: ምክንያቱም የዓድዋ ድል ለእነርሱ ቀላል አይደለም፤ አይረሱትም፤ በተለይ ኢትዮጵያ ላይ የተዛባ ዘገባ የሚያስተላልፉበት ምክንያት በፖለቲካዊ ታሪኩ ሳቢያ መሆኑ መታወቅ አለበት።

በተደጋጋሚ እንደሚታየው ኢትዮጵያን የሚበጠብጥ እና ገፅታዋን የሚያበላሽ ነገር ሲኖር እግር በእግር ተከትለው ይዘግባሉ:: ለተቀረው የዓለም ክፍል ሀገሪቱ የማትረባ፣ የወደቀች እና ቆሻሻ ሀገር ተደርጋ እንድትታይ ማድረግ ትኩረታቸው ነው:: ምክንያቱም መገናኛ ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች መጠቀሚያዎች ናቸው:: የዓባይ ግድብን አይነት ትላልቅ ፕሮጀክቶችን እንደስኬት አያቀርቡም::

መልካም ነገሮች ላይ ይጠፋሉ፤ አደጋ ሲደርስ አደጋውን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ደካማነት አጉልተው ለመውጣት ይሞክራሉ ብለዋል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሳምሶን መኮንን በበኩላቸው፤ የምዕራባዊያን መገናኛ ብዙኃን በጣም ትላልቅ መሆናቸውን በማስታወስ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በጦርነቱ ጊዜ ሲዘግቡ የነበረው ሁኔታ በብዙ መልኩ የሚተች መሆኑን ያብራራሉ::

አብዛኛዎቹ ቢ ቢ ስ፣ አልጄዚራ እና ሲ ኤን ኤን እንዲሁም የተለያዩ የህትመት ሚዲያዎች ማለትም ዋሽንግተን ፖስት እና ኒውዮርክ ታይምስ ስለ ኢትዮጵያ ሲዘግቡበት የነበረው መንገድ በጣም ችግር ያለበት እንደነበር እና ከጋዜጠኝነት መርህ አንፃር ሙያዊ ያልሆነ ሥራ ሲሰሩ ነበር ብለዋል:: በምሳሌ ሲያስረዱ፤ ጦርነት ሲዘገብ ሚዛናዊ መሆን እያለባቸው ግለሰቦችን ተጠቅመው የአንድ ወገን ዘገባን አስተላልፈዋል:: ከዚህ ባሻገር ጦርነት እንዲባባስ በማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት ለማሳጣት ሲሞክሩ ነበር ብለዋል:: ለአብነት ተከዜ ወንዝ ላይ የነበረውን ዘገባ ያስተላለፉበትን መንገድ ወቅሰው፤ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምርመራ አድርጎ አጥንቶ ያገኘውን ወደ ጎን በመተው ግለሰቦችን እንደምንጭ እየጠቀሱ ሲዘግቡ እንደነበር አስታውሰዋል::

የወቅቱ ዘገባቸው ኢትዮጵያ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ፈጥሮ፤ ባለስልጣናት ከሀገር ሀገር እንዳይዘዋወሩ እና የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲጣል ለማድረግ የሰሩትን ሥራ የሚረሳ አይደለም ይላሉ:: ኬንያ እና ኳተር ሆነው እየዘገቡ ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ሚዛናዊ ያልሆኑ ሽፋኖችን ሲያስተለልፉ ነበር ብለዋል::

ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሳምሶን ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ በኢትዮጵያ የተሻሉ ነገሮች መኖራቸውን በማስታወስ፤ አልፎ አልፎ የሚተላለፉ ዘገባዎች በተመሳሳይ መልኩ ከእውነት የራቁ እና ሚዛናዊነት የጎደላቸው ነበሩ:: ናይሮቢ ላይ ስምምነቱን በተመለከተ ለፌዴራል መንግስት እና ለሕወሓት ዕድል በመስጠት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሲዘግቡ የነበሩ መገናኛ ብዙኃን ቢኖሩም፤ የሰላም ስምምነቱ እንዳይሳካ እና አተገባበሩ ላይ ችግር እንዲፈጠር ልክ እንደቀድሞ ከጦርነቱ በፊት እንደነበረው አሁንም ጦርነት አለ በሚል መንገድ ሲዘግቡ የነበሩ መኖራቸው የሚዘነጋ አይደለም ይላሉ::

ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሳምሶን፤ መካድ የሌለበት ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን የራሳቸውን ሀገራት የፖለቲካ አቋምን የሚመስሉ ናቸው:: የሀገሩ የፖለቲካ እና የፖለቲካል ኢኮኖሚ ወሳኝ መሆኑን በመጥቀስ መገናኛ ብዙኃኑ ፈንድ በሚያደርጋቸው እና በሚያስተዳድራቸው አካል የተቀኙ ሊሆኑ እንደሚችሉ መረሳት የለበትም ባይ ናቸው::

ከትልልቅ መገናኛ ብዙኃን ጀርባ ትልልቅ መንግስታት አሉ የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን፤ መገናኛ ብዙኃኑ በየጊዜው እነርሱን የማገልገል ስራ ሲሰሩ ዘገባቸውም ከሙያው ያፈነገጠ የሚሆንበት አጋጣሚ መኖሩን ያስረዳሉ:: የመንግስታቸውን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አስፈፃሚዎች መሆናቸውን በማስታወስ፤ ጥሩም ሆነ መጥፎ ሲዘግቡ የመንግስታቸው ነፀብራቅ መሆኑ መታወቅ አለበት ይላሉ::

ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሳምሶን እንደሚያስረዱት፤ የአውሮፓውያን ጣልቃ ገብነት የሚታወቅ ነው:: በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በሩስያ እና ዩክሬን መሃል ጣልቃ ሲገቡ ታይተዋል:: በኢትዮጵያም ረገድ ጥቅማቸውን አስልተው የመካከለኛው ምስራቅ ወይም የምዕራብ ሀገራት መንግስታት ጣልቃ አይገቡም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ትልቅ ሀገር ናት:: የአፍሪካ ቀንድ ላይ መሆኗ እንድትፈለግ የሚስገድድ ነው:: በተጨማሪ ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ የህዝብ ቁጥር አላት:: ይህ ስድስት ወይም ሰባት የአፍሪካ ሀገራት አሊያም አስር የአውሮፓ ሀገራትን የሚያክል የህዝብ ቁጥር ያላት መሆኑም በራሱ በልዩ ሁኔታ እንድትታይ ያደርጋታል የሚል ግምት እንዳላቸው ያብራራሉ::

እንደረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሳምሶን ገለፃ፤ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ኢትዮጵያ ላይ ብዙ ጊዜ መጥፎ መጥፎ ላይ ብቻ የሚያተኩር ዘገባ የሚያስተላልፉት በምዕራባውያኑ የኢኮኖሚ ፍላጎት ምክንያት ነው:: የፖለቲካ ፍላጎትም ይኖራቸዋል:: በአፍሪካ ጠንካራ መንግስት እንዲፈጠረ አይፈልጉም፤ ይሄ የተለመደ መሆኑን እና ኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሀገሮች ላይም የሚፈፀም መሆኑን ያስረዳሉ:: ጅቡቲ አቀማመጧ (ጅኦ እስትራቴጂክ ሎኬሽኗ) ለፈረንሳይ ትልቅ ጠቀሜታ ስላላት ፈረንሳይ በዛች ሀገር ጠንካራ መንግስት እንዳይኖር ትሠራለች::

ፈረንሳይ ብቻ ሳትሆን አውሮፓውያኑ የአፍሪካ መንግስታት ጠንካራ በሆኑ ቁጥር የአውሮፓውያኑ የኢኮኖሚ ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ስለሚገባ፤ ጠንካራ መንግስት እንዳይፈጠር ትልቁን ሥራ የሚሠሩት በእነዚሁ መገናኛ ብዙኃናቸው መሆኑን ያመለክታሉ:: በውሸት ዜና አምባጋነን እያስባሉ፤ ጦርነት ሲፈጠር የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲኖር ተገንጣይ ሀይሎችን በመደገፍ በመገናኛ ብዙኃናቸው ወታደራዊ ግጭቶች ላይ ቤንዚል የማርከፍከፍ ስራን እንደሚሠሩም ተናግረዋል::

ሀብት ለመበዝበዝ እና የተዳከመች አፍሪካን ለመፍጠር በዓለም አቀፍ የፖለቲካ አዙሪት ውስጥ በመገናኛ ብዙኃን በተለያየ መንገድ እንደሚሠሩ የተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን፤ አሁን በመገናኛ ብዙኃኑ አሰራር ምክንያት አፍሪካ ውስጥ እውነተኛ ነገር ቢፈጠር እንኳ ሪፖርት ሲያደርጉ ሰዎች በተቀራኒው እንዲታዩ እያስገደደ መሆኑን አመልክተዋል::

ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ብዙ ልማቶች እና አመርቂ ስራዎች ቢሰሩም፤ ሽፋን አይሰጡም:: በየትኛውም መገናኛ ብዙኃን የሚያስተጋቡት በጦርነት የተሞላች አፍሪካ፤ በረሃብ የተዳከመች አፍሪካ፣ ዕርዳታ የሚያስፈልጋት አፍሪካ እያሉ የሚያቀርቡት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ አፍሪካን ለማጠልሸት ነው ይላሉ::

> **በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ብዙ ልማቶች እና አምርቂ ሥራዎች ቢሰሩም፤ ሽፋን አይሰጡም:: በየትኛውም መገናኛ ብዙኃን የሚያስተጋቡት በጦርነት የተሞላች አፍሪካ፤ በረሃብ የተዳከመች አፍሪካ፣ ዕርዳታ የሚያስፈልጋት አፍሪካ እያሉ የሚያቀርቡት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ አፍሪካን ለማጠልሸት ነው**

መገናኛ ብዙኃን ልማትን ለመምጣት የሚጠቅሙ ትልቅ መሳሪያዎች ናቸው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሳምሶን፤ ነገር ግን ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ለአፍሪካ ሲሆን የሚጠቀሙበት የተለየ ነው:: ይሄንን የሰላም ስምምነቱ ያመጣቸውን መልካም ነገሮች ምን ያህል ሽፋን እንዳልሰጡት በማየት ማረጋገጥ እንደሚቻል ያስረዳሉ::

መገናኛ ብዙኃኑ የመንግስታቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጦርነቱ እንዲቀጥል ፍላጎት ሲኖራቸው፤ ያለውን ግጭት ማስጮህ የሰላም ስምምነት ሲኖር ሰላምን ከማስተጋባት ይልቅ፤ በተቀራኒው የሚዘግቡበት ሁኔታ መኖሩንም ያመለክታሉ::

የወደፊቱን አስመልክቶ የሚናገሩት ዶክተር ደምመላሽ በበኩላቸው፤ በቀጣይ ኢትዮጵያውያን እጅ ለእጅ በመያያዝ ሀገሪቱን ወደፊት ማስኳዝ በሚቻልበት መንገድ ላይ ማሰብ አለባቸው:: በዲፕሎማሲው በተለይም በዲጂታል ዲፕሎማሲው፣ በማቴሪያል ዲፕሎማሲው፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በእርሻም ሆነ በተለያዩ ዘርፎች ትምህርት እና ምርምርን በማዘመን፣ ዜጎችን በማክበር፣ በመከባበር፣ ፖለቲካውን በማዘመን መስራት ቢቻል የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን አዘጋገባቸው ሁኔታ አሳሳቢ አይሆንም::

ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንን በመተው፤ የሀገሪቱን መገናኛ ብዙኃን ማዘመን እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ማድረግ ያስፈልጋል:: የሕትመት ሚዲያው፣ የብሮድካስት ሚዲያውም ሆነ የሶሻል ሚዲያው ዜናዎችን መስራት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ አንባቢ እና አድማጭ እንዲኖር መስራት አለባቸው ብለዋል።

ለጊዜውም ቢሆን ግን የተዛባውን የዓለም አቀፍ የሚዲያ ዘገባ ለመከላከል ቢያንስ ፖለቲከኞች እና ምሁራን ዲፕሎማሲውን ለማዘመን መስራት አለባቸው የሚል እምነት እንዳላቸውም ነው የጠቀሱት።

ምሁራኑ እንደገለፁት፤ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ስለኢትዮጵያ የሚዘግቡበት መንገድ የተዛባ እና ጥላቻ የተሞላበት ነው:: ይህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃኑን ከመሰረተው እና ከሚደግፍ መንግስት የመነጨ በመሆኑ ይህን ችግር ለማቃለል መፍትሔው በጊዜያዊነት የዲፕሎማሲ ሥራው ከላይ ትኩረት ማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሁሉም መስክ ውጤታማ ሥራን በማከናወን እና የሀገሪቷን ዕድገት በማረጋገጥ ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል::

ማህበራዊ

# ሴቶች

## መገለልና ድህነት በቃን ያሉት የሥጋ ደዌ በሽታ ተጠቂ እንስቶች

**ሰላማዊት ውቤ**



ወይዘሮ ብርቄ ንጋቱ በሥራ ሳይ

ወይዘሮ ብርቄ ንጋቱ ይባላሉ:: ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩቸውም ከትዳራቸው አምስት ልጆች አፍርተዋል:: አሁን ደግሞ የአምስት የልጅ ልጆች አያት መሆን ችለዋል:: ከልጆቻቸው አልፈው የልጅ ልጆቻቸውን በማስተማር ላይ ይገኛሉ:: ዛሬ ላይ ቀደም ሲል ይደርስ የነበረውን መገለል ተቋቁመው እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ሰርተው አምስቱንም ልጆቻቸውን በማስተማራቸው ልጆቻቸው የመንግስት ሠራተኞች ሆነውላቸዋል:: ወይዘሮ ብርቄ በስጋ ደዌ በሽታ የተጠቁት የስድስት ዓመት ልጅ ሆነው ነው:: ችግሩ የተከሰተው በልጅነት እድሜያቸው ስለነበር እንዴት እንደጀመራቸው አያስታውሱም:: ነገር ግን ቤተሰቦቻቸው ቶሎ ወደ ሕክምና ተቋም ባለማድረሳቸው በሽታው እየተባባሰባቸው እንደመጣ ይናገራሉ::

‹‹......በወቅቱ ቤተሰቦቼም ቢሆኑ ስለ በሽታው ምንም ግንዛቤ አልነበራቸውና አካል ጉዳቱ ደረሰብኝ›› ሲሉም ሁኔታውን ያስታውሱታል:: በሽታው ጉዳት ያደረሰው እጅና እግራቸውን ጨምሮ በሁሉም የሰውነት ክፍሎቻቸው ላይ ነው:: ሆኖም ደጋግመው ቢሆንም በፍፁም ከመሥራት እንዳላገዳቸው ያወሳሉ:: ወይዘሮ ብርቄ አካል ጉዳቱ ከደረሰባቸው በኋላ ነው ወደ አለርት ሆስፒታል ነው የሄዱት:: ምንም እንኳን ቶሎ ወደ ሆስፒታል ባለመሄዳቸው የሰውነት ክፍላቸው በበሽታው ቢጎዳም ሆስፒታል ከሄዱ በኋላ በተደረገላቸው ሕክምና የስጋ ደዌ በሽታ አምጪ ባክቴሪያ ከውስጣቸው መወገድ በመቻሉ ከበሽታው ነፃ ሆነዋል::

‹‹ባክቴሪያው ከውስጤ በመጥፋቱና ከበሽታው ነፃ በመሆኔ በእጅጉ ተደስቻለሁ›› የሚሉት ወይዘሮ ብርቄ ‹‹ ይህ መሆኑ ራሴን መቻል እንዳለብኝ እንዳውቅና የተስፋ ሕይወት እንዲኖረኝ አደረገኝ›› ሲሉም ከበሽታው ነፃ የመሆናቸውን ሁኔታ የፈጠረባቸውን ለስራ አነሳሽና አስደሳች ስሜት ያወሱታል:: ‹‹አሁን ከባክቴሪያው ነፃ ነኝ:: ምንም ዓይነት የሚሰማኝ ህመም የለም›› ሲሉም የውስጣዊ የሰውነት ጤንነታቸውን ሁኔታ ያስረዳሉ ''::

‹‹እኛ እኮ የአካል ጉዳት ነው ያለብን እንጂ ጤነኞች ነን›› የሚሉት ወይዘሮ ብርቄ ሆኖም የአካል ጉዳቱ ከመስራት እንደማያግዳቸውም በራስ በመተማመን መንፈስ ይገልፃሉ:: በሌላ በኩልም የስጋ ደዌ በሽታን አምጪ የሆነው ባክቴሪያ ከአቅም በላይ የሥራ ጫና ስለማይስማማው እሳቸውም አቅማቸው የፈቀደውን ይሰራሉ:: በዚህም የተለያዩ የእደ ጥበብ ስራዎች ምርት ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ::

ከዚህ የእጅ ጥበብ ሙያ ጥሩ ልምድ በማግኘትም ከሌሎች እንደሳቸው በበሽታው ከተጠቁ ሴቶች ጋር በማህበር በመደራጀት ቀጥታ ወደ ሥራ ለመሰማራት መቻላቸውን ያወሳሉ:: ይሄ ወይዘሮ ብርቄና ሌሎቹ የበሽታው ተጠቂዎች ወደ ሥራ የገቡበት ወቅት 2009 ዓ.ም ነበር:: በዚህ ወቅት 35 ሴቶች ሆነው ከአራት ወንድ አባላት ጋር ‹‹ክብነሽና ጓደኞቻቸው ዕደ ጥበብ ሥራ ሕብረት ሽርክና ማህበር›› የተሰኘውን ማህበራቸውን መሰረቱ:: ወይዘሮ ብርቄ የማህበሩ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ሆነው እየሰሩ ሲሆን ማህበሩን መመስረትና በማህበሩ ውስጥ በዕደ ጥበብ ሥራ የመስራት ልምድ ያላቸው መሆኑ ሥራው እንዳይከብዳቸው አስተዋጽኦ አድርጎላቸዋል:: ዛሬ ከየኪሳቸው ባወጡት 900 ብር የመሰረቱት ማህበር ካፒታል 500 ሺህ ብር ደርሷል:: ለመንግስት ግብር በመክፈልም እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ለአገራቸው ኢኮኖሚ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ::

ብዙዎቹ የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ሕክምናውን በተከታታይ በማግኘታቸውና በማህበር ተደራጅተው በጋራ በመሥራታቸው ከልመና መላቀቃቸውንም ያነሳሉ:: በበሽታው ምክንያትና በገጠማቸው የኑሮ ጫና ምክንያት ከዚህ ቀደም ልጆቻቸውን እንኳን የማስተማር አቅም እንዳልነበራቸው ይገልፃሉ:: አሁን ራሳቸው በመሥራት አቅም ከመፍጠራቸው ውጪ ከልመና ወጥተው ልጆቻቸውን ማስተማር መቻላቸውንም ይናገራሉ::

ወይዘሮ ሰውነት አእምሮ ከነዚህ እናቶች መካከል አንዷ ናቸው:: ተወልደው ያደጉት ደብረ ማርቆስ ሲሆን በሥጋ ደዌ በሽታ የተጠቁት ገና የሰላሳ ዓመት ወጣት ሳሉ ነው:: ወይዘሮ ሰውነት በበሽታው የተያዙ ሰሞን ፈጥነው ሕክምና ባለማግኘታቸው በእጅና እግራቸው ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት በሕብረተሰቡ በእጅጉ ይገለሉ የነበረ ሲሆን በማህበር፤ በዕድር፤ በዕቁብ በለቅሶ እንዳይሳተፉም ሆነው ስለመቆየታቸው ይናገራሉ:: በዚህም ሳቢያ ቀደም ሲል ወደ ትውልድ አገራቸው ደብረ ማርቆስ የመመለስ ሀሳባቸውንም እዛም የባሰ መገለል ይደርስብኛል በሚል ፍራቻ ትተውት ከነጉዳታቸው አለርት ሆስፒታል አካባቢ መኖር ጀመሩ:: ወይዘሮ ሰውነት ዕድሜያቸውን በውል ባያውቁትም ቢያንስ ስልሳውን መድፈናቸውን ይናገራሉ:: የማህበሩ መሥራችና አባልም ናቸው::

> ‹‹ሥጋ ደዌ ህክምና ካልተደረገለት አደገኛ እና ቋሚ የሆነ ጉዳት በቆዳ፣ በነርብ እና በአይን፤ በአፍንጫ ላይ ሊያደርስ የሚችል ነው››

በሽታው በእጅና በእግራቸው ላይ ከባድ ጉዳት አድርሶባቸው ቢያልፍም በአሁኑ ወቅት ሕክምና አግኝተው ከባክቴሪያው ነፃ ለመሆን ችለዋል:: ቁጭ ብለው ለዓይን የሚማርኩና የሚያስደስቱ የእጅ ጥበብ ሥራዎችን በሚያስደንቅ ሁኔታ ይሰራሉ:: ሦስት ልጆቻቸውንም ማሳደግና ለቁም ነገር ማብቃት ችለዋል:: አሁን ልጆቻቸው ከራሳቸው አልፈው እሳቸውን መደገፍ ጀምረዋል:: ወይዘሮ ሰውነት በማህበሩ ታቅፈው በዚህ ዓይነቱ የእጅ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ ይተዳደሩ የነበረው በልመና ሥራ እንደነበር ይናገራሉ::

‹‹እኛ የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች መሥራትና መኖር የምንችል የሕብረተሰብ ክፍሎች ነን›› የሚሉት ሌላዋ የማህበሩ መሥራች አባል ወይዘሮ እታገኝ መለሰ አባላት ማህበሩን የመሰረቱት በዕድር፤ በእቁብ፤ በማህበርና በተለያዩ ሁኔታዎች ከሕብረተሰቡ እንዳይገለሉና መገለል የሚያደርስባቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ተቋቁመው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ብሎም አገራቸውን ለመጥቀም በማሰብ ነው ይላሉ::

ወይዘሮ እታገኝ ትውልድና ዕድገታቸው ጎንደር ገጠር ከተማ ውስጥ ነው:: በበሽታው የተያዙት ገና የ11 ዓመት ልጅ ሆነው ሲሆን ለህክምና ወደ አዲስ አበባ ያመጧቸው የአባታቸው ወንድም ናቸው፤ በወቅቱም አለርት ሆስፒታል ህክምናቸውን ከመከታተላቸውም በላይ እስከ 11ኛ ክፍል ድረስም ትምህርት አስተምረዋቸዋል:: በትምህርት ላይ እያሉ ጭምር ከባድ የጉልበት ሥራዎችን በመሥራት ነበር እራሳቸውን የሚያስተዳድሩት:: ሥራው ከባድ በመሆኑና የበሽታው ሐኪሞች ከባድ ሥራ መሥራት በሽታውን እንደሚያባብሰው ሲናገሩ ሰምተናል የሚሉ ሰዎች ስላስፈራሯቸው ባክቴሪያውን በመቀስቀስ ዳግም በበሽታው እጠቃለሁ የሚል ስጋት ነበራቸው:: በማህበር ተደራጅተው መሥራታቸውና ከከባዱና ከሚያሰቃየው የጉልበት ሥራ መላቀቃቸው በጫናው ምክንያት ይደርስባቸው ከነበረው ስጋታቸው ገላግሏቸዋል:: ወይዘሮ እታገኝ አሁን ላይ በሰውነት ክፍላቸው ላይ ምንም ጉዳት ስለሌለ የበሽታው ተጠቂ ባይመስሉም በህክምና ባክቴሪያው እንዳለባቸው ስለተረጋገጠ ብሎም የአካባቢው ነዋሪዎች በሽታው እንዳለባቸው ስለሚያውቁ የማህበሩ መሥራች አባል ሆነው በመታቀፍ ስራዎችን እየሰሩ በየወሩ የአንድ ሺህ ብር ደሞዝ ተከፋይ ሆነዋል:: ማህበሩን እንዲያደራጁ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸውን የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ብሔራዊ ማህበርም ደጋግመው ያመሰግናሉ:: ‹‹በማህበር መደራጀት የቻልነው ብሄራዊ ማህበሩ በመኖሩና በእሱ ታቅፈን መንቀሳቀስ በመቻላችን ነው›› ሲሉ ሀሳባቸው ያሳርጋሉ::

አቶ ተስፋዬ ታደሰ የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ብሔራዊ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ ማህበሩ በሰባት ክልል ከ70 ቅርንጫፍ ማህበራትን አደራጅቷል:: እንደ አገር ከ20 ሺ የስጋ ደዌ በሽታ ተጠቂዎችን አቅፏል:: በበሽታው ከተጠቁት ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ሴቶች መሆናቸው ደግሞ ማህበሩ ሁሉም ላይ ቢሰራም ሴቶች ላይ የበለጠ እንዲሰራ አድርጎታል ባይ ናቸው::

አብዛኞቹ አባላት ሴቶች ሊሆኑ የቻሉበት ምክንያት አንድም ሴቶች እንደወንዶቹ መረጃ የማግኘት ሰፊ ዕድል ስለሌላቸውና የበሽታውን ምንነት በውል ስለማያውቁት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቤት ውስጥና በተለያየ ቦታ ባለባቸው የሥራ ጫና ምክንያት ቶሎ ወደ ሕክምና ስለማይሄዱ ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ መረጃው ቢኖራቸውና መሄድ ቢፈልጉም ከትራንስፖርት ወጪ ጀምሮ ለሕክምናውና የሚያስፈልገውን ወጪ የሚሸፍን አቅም የላቸውም::

በሽታው የእግዚአብሔር ቁጣ ነው፤ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል ለሚለው የተዛባ አስተሳሰብ እንዳይጋለጡ ፈርተው ወደ ሕክምና የማይሄዱበት አጋጣሚም ቀላል አይደለም:: በዕቁብ፤ በዕድር፤ በማህበርና በለቅሶ መገለሉንም ስለሚፈሩት ራሳቸውን ይደብቃሉም:: በአጠቃላይ ወንድም ሆኑ ሴት የበሽታው ተጠቂዎች የሚደርስባቸውን መድሎና መገለል በመፍራት ለዘመናት ራሳቸውን ከሕብረተሰቡ አርቀው በቤተክርስቲያን ጥጋት፤ በየሥርቻው እንዲሁም ለመኖር በማይመቹና ለሰው ልጅ በማይገቡ ቆሻሻ ሥፍራዎች በልመና እና በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ በጉስቁልና በመኖር የከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ሰለባ ሆነው ቆይተዋል:: በተዛባ የሕብረተሰቡ አመለካከት ምክንያትም አሁን ድረስ ብዙዎቹ ራሳቸውን ከህብረተሰቡ በማግለል በከባድ የኑሮና ስነ ልቦና ጫና ውስጥ መሆናቸውንም አቶ ተስፋዬ ያነሳሉ::

ማህበሩ ይሄን ችግራቸውን ለመቅረፍ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት በሥጋ ደዌ በሽታ የሚመጡ የአካል ጉዳቶችን በመቀነስ፤ በበሽታው ምክንያት የሚመጡትን አካላዊ፤ መንፈሳዊ፤ ማህበራዊ መገለሎችን ለማስቀረት እንዲሁም አዳዲስ የሥጋ ደዌ በሽታ እንዳይፈጠር ቅድመ ጥንቃቄ የሚደረግበት ግንዛቤ በመፍጠር ሲሰራ መቆየቱንም አቶ ተስፋዬ ይገልጻሉ::

ብሔራዊ ማህበሩ የወፍጮ ቤት፤ በዓመት እስከ ስድስት ሚሊዮን ብር የሚያስገኝ የሚከራይ ቤት፤ የከብት እርባታና የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ በአዲስ አበባ በሀዋሳ፤ በኮምቦልቻ ፤ በባህር ዳር፤ በጎጃም ሸበል በረንታ እንዲሁም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙና በበሽታው ለተጠቁ አባላቱ በማህበራዊ ኑሯቸው ወደኋላ ለቀሩ ድጋፍ የሚያደርግበት ሁኔታ አለ:: አብዛኞቹን በጥቃቅንና አነስተኛ በማደራጀትም ወደ ሥራ አሸጋግሮ አምራች አድርጓቸዋል:: በዚህም ብዙ ሴቶች እንደማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል ሰርተው መኖር፤ ቤተሰባቸውን ማስተዳደር በተለይም ደግሞ ልጆቻቸውን ማስተማር ችለዋል::

ተጠቂዎቹ በመገለላቸው ምክንያት ከወደቁበት ከቤተክርስቲያን መጠለያና ከአልባሌ ሥፍራዎች በማውጣት ቤት መሥሪያ ቦታ፤ እንዲሁም የቀበሌና የኪራይ ቤት ባለቤቶች በመሆን ከሕብረተሰቡ ተቀላቅለው በነፃነት እንዲኖሩ እንዲሁም ተከታታይ ሕክምና እንዲያገኙ መደረጉንም ይናገራሉ::

‹‹ማህበሩ ከመመስረቱ በፊት አካል ጉዳቱ ባስከተለባቸው ጫና ምክንያት ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ የማይችሉ ወላጆች ቁጥር ከፍተኛ ነበር›› የሚሉት ሥራ አስኪያጁ ማህበሩ ከተመሰረተ በኋላ ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት መላክ የሚያስችል አቅም ስለፈጠረላቸው ከትምህርት የመገለል ችግር ተቀርፎላቸዋል:: በዚህም ልጆቻቸው በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተምረው በመመረቅ ራሳቸውን ችለው እየኖሩና ቤተሰባቸውን እያገዙ ይገኛሉ::

በሴቶች ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች የአድቮካሲና መብት ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሲሳይ ጥላሁን መሥሪያ ቤታቸው ለሥጋ ደዌ በሽታ ተጠቂዎችም እንደማንኛውም አካል ጉዳት የእኩል ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት መብታቸው እንዲከበር በትኩረት እየሰራ ይገኛል:: ሥራውን ከማህበሩና ከተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራው ሲሆን ሰብዓዊ መብቶቻቸው እንዲከበርም ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል:: በተለይ መገለልና መድሎ ቀርቶላቸው ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው በሚኖሩበት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል:: እንደ መጠለያ፤ ምግብ ያሉና ሌሎች መሰረታዊ ፍላጎታቸው እንዲሟሉላቸው በየደረጃው ይሰራል:: ሕክምናውን ተከታትለው ከበሽታው ነፃ እንዲወጡም እየተደረገ ይገኛል ::

‹‹ሥጋ ደዌ ህክምና ካልተደረገለት አደገኛ እና ቋሚ የሆነ ጉዳት በቆዳ፣ በነርብ እና በአይን፤ በአፍንጫ ላይ ሊያደርስ የሚችል ነው›› የሚሉት አቶ ሲሳይ በዚህ ምክንያት ሕክምና እንዲያገኙ ትኩረት እንደሚያደርግ ሁሉ በበሽታው ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ከማህበሩና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የዊልቸርና የተለያዩ ለእንቅስቃሴ የሚያመቹ ድጋፎችም ይደረጋሉ:: በተለያዩ ማህበራት ተደራጅተው የኢኮኖሚ ችግራቸውን እንዲቀርፉም ይሰራል:: በተለይ መገለልና መድሎ ተወግዶላቸው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው እንዲኖሩና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በመፍታት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረጉ ረገድ በትኩረት እየተሰራ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ለውጥ ቢመጣም ገና ብዙ መሰራት የሚፈልግና የሚቀር ስራ መኖሩን ይናገራሉ::

የሥጋ ደዌ ከቀደምት የቻይና፣ የግብፅ እና የህንድ ሥልጣኔ ጀምሮ የነበረ ሲሆን የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ለዘመናት በሚኖሩበት ማህበረሰብና ቤተሰቦቻቸው የመገለል አደጋ ሲደርስባቸው ቆይቷል። የመጀመሪያው የሥጋ ደዌን የሚጠቅስ ጽሁፍ የተጻፈው 600 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን የሥጋ ደዌ ህመምተኛ በመልቲ ድራግ ትሪትመንት ለስድስት ወራትና ለ12 ወራት ታክሞ መዳን ይችላል። ኤምዲቲ መውሰድ ከጀመሩ በኋላ ህሙማን ሥጋ ደዌን ወደ ሌላ ሰው እንደማያስተላልፉ ከበሽታው ጋር ተያይዘው የወጡ ጽሑፎች ይጠቅሳሉ::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የዛሬ 55 ዓመት በ1961 ዓ.ም በያዝነው ጥር ወር የታተሙትን የአዲስ ዘመን ጋዜጦች ለዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን ለመዳሰስ ሞክረናል።በአሁኑ ወቅት እንደሚታየው የሸቀጦችና ቁሳቁሶች ዋጋ መናር በዚያ ዘመንም እንደነበር የሚያስታውሰን አንድ ዘገባ ግሽበቱን ለመቆጣጠር ስለተወሰዱ እርምጃዎች የሚነግረን አለው።በወቅቱ የተወሰደው ርምጃ በዘመናችን የሲሚንቶ ዋጋ መናርን ለመቆጣጠር የተወሰደውን ርምጃ ይመስላል። ዛሬ በውጭ ምንዛሪ የምንሸምተው የምግብ ዘይት በወቅቱ በሀገር ውስጥ ፋብሪካ ለማዳረስ ፋብሪካ በማቋቋም ስለሚደረግ ጥረትም ተዘግቦ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ አሳማ ሰው ነክሳ አቆሰለች የሚልን አንድ ዘገባና ሌሎችም ግርምትን የሚፈጥሩ ዘገባዎችን ለትውስታ ያህል አቀርበናል።

### ሽማግሌው ሞተው ተገኙ

አድዋ፤(ኢ-ዜ-አ-) በአድዋ አውራጃ ግዛት በአዲ አቤቶ ወረዳ እንዳ ማርያም ውኢላ በተባለው ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ለ፳፭ አጥቢያ ለጊዜው አድራሻቸውና ስማቸው ያልታወቀ አንድ ሽማግሌ ሞተው ተገኙ።

የሰውየውን መሞት የቀበሌው ሕዝብ ለፖሊስ ጣቢያ ካመለከተ በኋላ ፤አስከሬኑ አዲአቡን ወደሚገኘው መንገሻ ዮሐንስ ሆስፒታል ተወስዶ ሽማግሌው በሰው እጅ ያልሞቱ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ ፤ደብረማርቆስ ቤተክርስቲያን ተቀብሯል። የሟቹ ዕድሜ ፸፰ ዓመት እንደሚሆን ተገምቷል።

(ጥር 7 ቀን 1961 ከታተመው አዲስ ዘመን)

### አሳማ ሰው ነክሳ አቆሰለች

ነቀምቴ ፤(ኢ-ዜ-አ) በአንዲት ከጫካ ውስጥ የወጣች አሳማ የተነከሰ ሰው በሆስፒታል በሕክምና ላይ ይገኛል።ይኸው በአሳማዋ ተነክሶ የስብራት አደጋ የደረሰበት ሰንበቶ በጂጋ የተባለው ሰው ሲሆን፣አደጋውም ሊደርስ የቻለው አቶ በየነ ኪትል ይባሉ የነበሩት የነቀምቴ ከተማ ነዋሪ በሞቱበት ዕለት በለቅሶ ላይ እንዳለ ነው።

በአሳማዋ በድንገት ከጫካ ውስጥ ወጥታ በለቀስተኞቹ መካከል እንደታየች አልቃሾቹም በአውሬዋ ምክንያት ተደናግጠው ሲሯሯጡ ሰንበቶ በጂጋን አባርራ የግራ እግሩን ባቱ ላይ በመንከስ ስብራት አድርሳበታለች።

ከዚህም በቀር አሳማዋ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ለማድረስ ስትሞክር በሥፍራው የነበረው ሕዝብ በዱላ ደብድቦ በጦር ወግቶ ገድሏታል።

በአሳማዋ የተነከሰው ሰው ለሕክምና ወደ ነቀምቴ ተፈሪ መኮንን ሆስፒታል ተልኮ በሕክምና ላይ የሚገኝ መሆኑን የነቀምቴ ከተማ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ የአሥር አለቃ ዓለሙ ገለጡ።(ጥር 11 ቀን 19 61 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)

### ፩ሚሊዮን ፪፻ ሺህ ብር ፈጅቷል የዘይትና የሣሙና ፋብሪካ በቅርቡ ሥራ ይጀምራል

አዲስ አበባ ፣(ኢ/ዜ/አ) ፩ሚሊዮን ፪፻ ሺህ ብር የፈጀው የዘይትና የሣሙና ፋብሪካ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሥራውን ይጀምራል።በደብረ ዘይት መንገድ በንፋስ ስልክ ቀበሌ በመሠራት ላይ የሚገኘው የፔትራቶስ የዘይትና የሣሙና ፋብሪካ የግል ኩባንያ በ፩ሚሊዮን ፪፻ ሺህ ብር የሚያሠራው አዲሱ የፋብሪካ ሕንፃና የኢንዱስትሪ መሣሪያ በቅርብ ጊዜ መደበኛ ሥራውን ይጀምራል።

በ፲፱፻፵፰ ዓ ም በ፴ ሺህ ብር ካፒታል የተቋቋመውና አሁን በተከፈለ ፬፻ ሺህ ብር ካፒታል የሚካሄደው የገብርኤል ፔትሮቶስ የዘይት ፋብሪካ ፳፭ ቋሚ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን ፤ አዲሱ ፋብሪካ ሥራውን ሲጀምር ፤የሠራተኞቹ ብዛት ፪፻ለማድረስ ያቀደ መሆኑን ባለንብረቱ ሙሴ ገብርኤል ፔትራቶስ ገልጠዋል።

ይህ ፋብሪካ ከተቋቋመ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ፲፫ ዓመት ሙሉ ይሠራ የነበረው የምግብ ዘይት ከኑግ ብቻ ሲሆን ፤ወደፊት ግን አዲስ በሚያስመጣው መሣሪያ ሪፋይነሪ ከተልባ ፤ከጐመን ዘርና ከኑግ የምግብ ዘይቶችን እየሰራ ለገበያ የሚያቀርብ መሆኑን ሥራ አስኪያጁ ገልጠዋል።

ፋብሪካው ከአሁን በፊት ከራሱና ጥቃቅን ዘይት ፋብሪካዎች እየገዛ በዓመት ፷ሺህ ቶንስ የኑግ ጭማቂ (አተላ) ወደ ዴንማርክ፣ ሆላንድና ጀርመን እየላከ ይሸጥ እንደነበር ገልጠው ወደፊት ግን በብዛትና ክብደት ለማሻገር ማቀዱን ሥራ አስኪያጁ አረጋግጠዋል።

የአዲሱ ፋብሪካ ሕንፃ ያረፈው በ፺፪ ሜትር ካሬ ቦታ ላይ ሲሆን ፤የግቢው ስፋት ደግሞ ፮ሺህ፺፪ ሜትር ካሬ ነው።ለአዲሱ ፋብሪካ ከተደረገው የ፩ሚሊዮን ፪፻ሺህ ብር ውስጥ ፪፻፺ሺህ የፋብሪካው ሕንፃ ማሠሪያ ሲሆን የቀረው ደግሞ ለአዲ የዘይትና የሣሙና መሥሪያ መግዣ የወጣ ነው። (ጥር 6 ቀን 19 61 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)

### ነጋዴዎች እንዲያውቁት ስኳር በቀድሞ ዋጋ እንዲሸጥ ማስገንዘቢያ ወጣ

(ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ)

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዋጋ መቆጣጠሪያ ክፍል እለታዊ ቁጥር ክፍል በሚያደርግበት ወቅት የስኳር ዋጋ ጨምሮ መገኘቱን ለመረዳት ስለቻለ ፤ጉዳዩን ካጣራ በኋላ ፤የስኳር ሽያጭ እንደቀድሞው እንዲሆን ለፋብሪካ ለነጋዴዎች ማስገንዘቢያ አወጣ።

ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል የተሰጠው ዜና እንደሚያመለክተው ፤ የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ወደ ንግድና ኢንዱስትሪ ተጠርተው ፤ ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተደርጓል።የስኳር ዋጋም ስለጨመረበት ምክንያት ምክትል ሥራ አስኪያጁ የሰጡት ማስረጃ አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱና ተገቢው የአሠራር ዘዴ ባለመከተሉ፤ ኩባንያው የቀድሞውን ዋጋ ሳይለውጥ እንዳይሸጥ ተገቢ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል።

ከእንግዲህ ወዲህ ከዚህ በላይ የተሰጠው መግለጫ የሚያፈርስ ሌላ ማሳሰቢያ እስከሚወጣበት ጊዜ ድረስ የስኳር ዋጋ ያለምንም ጭማሪ ለሕዝብ እንዲሸጥ የስኳር ነጋዴዎች ሁሉ እንዲያውቁት የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ትናንት በሰጠው መግለጫ ላይ አስገነዘበ።

ወደፊትም ስለዋጋው ምናልባት ለውጥ ቢኖር ፤ጉዳዩን በደንበኛው አጥንቶ ውሳኔውን የሚሰጠው ይኸው የሚኒስቴር መ/ቤት መሆኑን በመጥቀስ ፤ይህን ትዕዛዝ ባለማክበር፤ ማንኛውም የስኳር ነጋዴ ከተለመደው ዋጋ በላይ ስኳር ሲሸጥ ቢገኝ ተገቢው ርምጃ የሚወሰድበት መሆኑን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ትናንት አስታውቋል።

**(ጥር 10 ቀን 1961 ከታተመው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ



## በርካታ ሕይወትን ያጠፋው የቱርክ እና ሶሪያ ርዕደ መሬት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ማዕከላዊ ቱርክ እና ሰሜን ምዕራባዊ ሶሪያ ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በመከሰቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ህይወታቸውን ማጣታቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

በርዕደ መሬት መለኪያ (ሬክተር ስኬል) 7 ነጥብ 9 ሆኖ የተመዘገበው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በርካታ ህንጻዎችን በማፈራረሱም በፍርስራሽ ሥር ያሉ ሰዎችን የማትረፍ ርብርቡ ቀጥሏል።

አደጋው በምሽት መድረሱም የነፍስ አድን ሥራውን ፈታኝ ማድረጉ የተነገረ ሲሆን ኢርደም የተባለ የቱርኳ ጋዚያንቴፕ ከተማ ነዋሪ “በ40 ዓመት ውስጥ እንደዚህ አይነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም” ብለዋል።

“በጋዚያንቴፕ ከተማ አንድም ሰው በቤቱ ውስጥ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፤ ሁሉም ከቤቱ እየወጣ ሸሽቷል” ሲልም የአደጋውን አስከፊነት ገልጿል።

የቱርክ የአደጋ መከላከል ተቋም በአደጋው እስካሁን የ76 ሰዎች ህይወት ማለፉን የገለጸ ሲሆን ከ440 በላይ ሰዎችም መቁሰላቸውንና የሟቾቹ ቁጥር ማሻቀቡ እንደማይቀር ገልጿል።


በህንጻዎች ፍርስራሽ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ለማትረፍ ግን ርብርቡ መቀጠሉን ነው የቱርክ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትር ሱሌይማን ሶልዩ ለጋዜጠኞች የተናገሩት። አንካራ አለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግላት የጠየቀች ሲሆን፤ በቀጣይ ሊከሰት ለሚችል አደጋም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አዛለች።

በሶሪያም በሃማ፣ አሌፖ እና ላታኪያ ግዛቶች ከ100 በላይ ሰዎች በርዕደ መሬቱ ምክንያት ህይወታቸውን ማጣታቸውን የሀገሪቱ ብሄራዊ የዜና ወኪል ዘግቧል።

በ12 አመቱ የሶሪያ ጦርነት ተደጋጋሚ ጉዳት ያስተናገዱ ቤቶች በፍጥነት ወደ ፍርስራሽነት ተለውጠዋል ነው ያሉት የአይን እማኞች።

ንዝረቱ እስከ ሊባኖስ እና ቆጵሮስ ድረስ የተሰማው ርዕደ መሬት በአንካራም ሆነ በቤሩት ያደረሰው ጉዳት እንደሌለ ተገልጿል። ቱርክ ለመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ከፉኛ ተጋላጭ ከሆኑ ሀገራት መካከል አንዷ ናት።

በፈረንጆቹ 1999 ኢዝሚት በተሰኘች ከተማ የደረሰ ርዕደ መሬት ከ17 ሺህ በላይ ሰዎችን ህይወት መንጠቁ የሚታወስ ነው። በ2011ም በምስራቃዊቷ ቫን ከተማ ከ500 በላይ ሰዎችን ህይወት የቀጠፈ ርዕደ መሬት መከሰቱን ሬውተርስ በዘገባው አውስቷል።



## የቻይና ተንሳፋፊ የስለላ ፊኛ በደቡብ አሜሪካ እንደገና መታየቱ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሁለተኛው የቻይና ተንሳፋፊ የስለላ ፊኛ በደቡብ አሜሪካ መታየቱ ተገለጸ።

ከሰሞኑ ንብረትነቱ የቻይና የሆነ ተንሳፋፊ የስለላ ፊኛ ወደ አሜሪካ እና ካናዳ ከተሞች መግባቱን ተከትሎ በሁለቱ ሀገራት መካከል ውጥረት ነግሶ ቆይቷል።

በዚህ ተንሳፋፊ ፊኛ ምክንያትም ቻይናን ሊጎበኙ የነበሩት የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ጉዟቸውን ወደሌላ ጊዜ ለማዛወር ተገደዋል።

ዋሽንግተን ወደ አየር ክልሏ የገባው የቻይና ተንሳፋፊ ፊኛን ተኩሳ መትታ የጣለች ሲሆን ድርጊቱ በአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እንደተፈጸመ ሮይተርስ አስነብቧል።

ቻይና በበኩሏ ሰው አልባ እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያለመ ተንሳፋፊ ፊኛ ወደ አየር መላኳን ገልጻ በአሜሪካ መመታቱን አውግዛለች።

የአሜሪካ ሪፐብሊካን ፖለቲከኞች በበኩላቸው የፕሬዚዳንት ባይደን አስተዳደር ተነሳፋፊ ፊኛው ለቀናት በአሜሪካ አየር ክልል ውስጥ ከገባ በኋላ ለቀናት መጠበቃቸውን ተችተዋል።

አሁን ደግሞ ተመሳሳይ የሆነ የስለላ ተንሳፋፊ ፊኛ በደቡብ አሜሪካዊቷ ኮሎምቢያ አየር ክልል ውስጥ የቻይና ንብረት የሆነ ፊኛ መገኘቱ ተገልጿል።

የኮሎምቢያ መንግስት ጉዳዩን እየተከታተለ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፤ የቻይና ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በበኩሉ፣የተባለው ተንሳፋፊ ፊኛ የእሷ መሆኑን እና ባልታወቀ ምክንያት ወደ ደቡብ አሜሪካ እና ካሪቢያን ሀገራት መጓዙን ጠቅሳለች።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ሊዮልድ ኦስቲን በቻይና ድርጊት መበሳጨታቸውን ገልጸው፤ ቤጂንግ በተንሳፋፊ ፊኛዎች አማካኝነት የአሜሪካንን ስትራቴጂካዊ ቦታዎችን ለመሰለል ሞክራለች ብለዋል።

ቻይና በበኩሏ ፊኛዎቹ መደበኛ መረጃዎችን ለማግኘት መሰማራታቸውን ገልጻ፣ የአሜሪካ ድርጊት ግን ዓለም አቀፍ መደበኛ ድርጊቶችን የሚጎዳ እንደሆነ አስታውቃለች።

ዜና

# የተገኘው ሰላም ወደመልካም ዕድል እንዲቀየር ሕዝቡ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይገባል

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የተገኘው ሰላም ወደመልካም ዕድል ተቀይሮ በአካባቢው የተሻለ የልማት እና የማኅበራዊ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ሕዝቡ ግምባር ቀደም ሆኖ ሰላሙን ሊጠብቀው እንደሚገባ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አሳሰበ። ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ትልቅ ውጤት እንደሚጠበቅም አስታውቋል።

ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይለ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ የተገኘው የሰላም ጅማሮ እንዳይቀለበስ ሕዝቡ ግምባር ቀደም ሆኖ ሊጠብቀው ይገባል።

ከቆየንበት የሰላም እጦት ወጥተን ወደ ሰላም ሁኔታ በመግባቱ በተለይ ለትግራይ ሕዝብ ድል መሆኑንና ትዴፓም እንደ ፓርቲ ለዚህ ሰላም የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ከተገኘው የሰላም ዕድል ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብ ነቅቶና ተደራጅቶ ከጠበቀ የጥቅመኛ ፖለቲከኞች መጠቀሚያ አይሆንም ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ አብዛኛው ወጣት ሰላሙን ነቅቶ በመጠበቅ ላይ እንደሚገኝና የሰላም ሂደቱ ወደመልካም ዕድል ተቀይሮ የተሻለ እድል እንዲገኝ ፍላጎት አለው ብለዋል። ‹‹የመጣንበት መንገድ አክሳሪ ቢሆንም ከውድቀት ተምረን ቆም ብለን በማሰብ




ወደሚያዋጣን መንገድ መሸጋገሪያ ልናደርገው ይገባል›› ሲሉም አክለዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅት በመከላከያና የሰላም ኮሚቴ ስር የሚገኙ ሽረ፣ አክሱምና በዚያ አካባቢ የሚገኙ ቦታዎች የተሻለ የሰላም፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እያከናወኑ የሚገኙ እንደሆነ በመጥቀስ፤ በቅርቡም የትዴፓ አባላት በቦታው በመገኘት የተገኘውን ሰላም ማረጋገጣቸውን ተናግረዋል።

# ዩኒቨርሲቲው በአማራ ክልል እንሰትን ለምግብነት ለማላመድ እየሠራ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በአማራ ክልል እንሰትን ለምግብነት የማላመድ ሥራ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የፕሮጀክት ቀረጻና ትብብር ዳይሬክተር ዶክተር አበበ በላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በመተባበር እንሰትን ለምግብነት የማላመድ ፕሮጀክት ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል።

ፕሮጀክቱ ለአንድ ዓመት የሚዘልቅና በስምንት ወረዳዎች የሚተገበር ፓይለት ፕሮጀክት መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር አበበ፤ እስካሁን ድረስ በአራት ወረዳዎች ላይ የትግበራና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ተጀምሯል። በቀጣይነት ከሌሎች በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና ከክልሉ መንግሥት ጋር በመነጋገር ሥራውን ለማስፋት እንደሚሠራ አመላክተዋል።

ከእንሰት የሚዘጋጁ ምግቦች ከፍተኛ የንጥረ ምግብ ይዘት ያላቸው በመሆኑ በክልሉ በስፋት የሚስተዋለውን የሕጻናት መቀንጨር ችግር ለመቅረፍ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቁመው፤ እንሰት ለመልማት ብዙ ቦታ የማይፈልግና ከሌሎች ሰብሎች ጎን ለጎን ሊሠራ የሚችል በመሆኑ አርሶ አደሩ እንሰትን እያለማ በመመገብና ለገበያ በማቅረብ ሕይወቱን ማሻሻል እንደሚችል ገልጸዋል።

በተጨማሪም የአረንጓዴ ልማትን ለማሳደግም ለሚሠራው የማይተካ ሚና እንዳለውም ጨምረው ጠቅሰዋል።

እንሰት በተለያዩ አገሪቱ ክፍሎች በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በስፋት ለምግብነት የሚውል መሆኑን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፤ በአማራ ክልልም ተክሉን በስፋት በማልማት የአፈርን ለምነት ለማስጠበቅ አካባቢን



ዶክተር አበበ በላይ

ለማልማት፣ ለሽያጭ፣ ለቃጫ ምርት፣ ለቡላ፣ ለአረቄ፣ ገንፎ፣ ዳቦ ቆሎ፣ የጾምና ፍስክ ፍርፍር ማዘጋጀት እንደሚቻልም አቶ ባወቀ ጥሩነህ አክለው ገልፀዋል።

ፕሮጀክቱን ለመተግበር በተለያዩ አካባቢዎች ቡድን መቋቋሙን አመላክተው፤ ከልማት ባንክ በተገኘ ሁለት ሚሊዮን ብር ድጋፍና በዩኒቨርሲቲው ትብብር ተግባራዊ ይደረጋል። በቀጣይነትም የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ሥራውን የማስፋት ተግባራት እንደሚከናወኑ ገልጸዋል።

እያንዳንዳችን የምናከናውናቸው ተግባራት ሲደመሩ የሕዝባችንን ሕይወት ለመለወጥ ያስችለናል ያሉት ዶክተር አበበ፤ ለዚህ ፕሮጀክት መሳካትም ሁሉም ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

እንሰት በጥቂት ቦታ ላይ ሰፊ ምርት መስጠት የሚችል መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ከአንድ ሄክታር መሬት እስከ 610 ቶን ድረስ ምርት እንደሚገኝም ተጠቁሟል።

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

## ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ቤተሰብ የሚጠበቅበትን ማኅበራዊ ኃላፊነት እንዲወጣ በቂ ትኩረት አለመሰጠቱና መዘዙ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 3 ‹‹ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።›› በሚል የተቀመጠው ድንጋጌ ቤተሰብ ለአንድ ማኅበረሰብ ያለው ‹መሰረትነት› ተፈጥሯዊ መሆኑንና ያለበትንም ኃላፊነት በማጉላት ከኅብረተሰቡም ሆነ ከመንግሥት ጥበቃ ሊያገኝ እንደሚገባው ይገልጻል።

ሆኖም ሕገ መንግሥቱ ከጸደቀበት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት 28 ዓመታት ቤተሰብን የተመለከቱ የማኅበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች እና ሌሎች ፕሮግራሞች ተዘንግተው ኖረዋል። በተለይ ቤተሰብ በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ጥበቃ በበላይነት እና በእኔነት ስሜት ተከታትሎ የሚያስፈጽም ተቋም አልነበረም። በዚህም የተነሳ የህብረተሰብ መሰረት የሆነውና ትውልድን የማስቀጠል ኃላፊነት ያለበት ይህ ማህበራዊ ተቋም በቂ ትኩረት ስላልተሰጠው ተገቢ ሚናውን እየተወጣ ካለመሆኑም በላይ አባላቱ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲጋለጡ ይስተዋላል።

ነገር ግን ቤተሰብ መንግሥት የቤተሰብን ማኅበራዊ ደህንነት ለማጠናከር በሚዘረጋቸው ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን፣ ለማህበራዊ ችግሮች እንዳይጋለጥና አባላቱ እንዳይበተኑ ተገቢው ጥበቃ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት አለው። ቤተሰብን በተመለከተ ትኩረት አግኝተው ሊሠራባቸው የሚገቡ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ መነሻ የሆኑ ትልልቅ ጉዳዮች አሉ። እነኚህ ጉዳዮች በአንድ ሀገር የእድገት እና የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሰረት መሆኑን አጉልተው ያሳያሉ።

ስለዚህ ቤተሰብ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኝ እና ሕገ መንግሥታዊ መብቱ እንዲከበር ለማስቻል የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014፤ ‹‹ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ ዋና መሠረት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ በተግባር ለማዋል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ከሚመለከታቸው ክልላዊ መንግሥት አካላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይነድፋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤›› በሚል



**አቶ ተስፋዬ ሮበሌ፤**

ለሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት ይሰጣል።

ሚኒስቴሩም በአዋጁ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት የቤተሰብን ማኅበራዊ ደህንነት ለማጠናከርና ለማስጠበቅ፣ ቤተሰብ እንደ ህብረተሰብ መሰረትነቱ ተገቢ ሚናውን መወጣት እንዲችል፣ ከሚገጥሙት ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ነፃ እንዲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሥራ ክፍል በማደራጀት፣ የሰው ኃይል በመመደብ እና ክልሎችም በተመሳሳይ የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዲችሉ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአረጋዊያንና ቤተሰብ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ይናገራሉ።

ከሰሞኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ “የቤተሰብ መልካም እሴቶች አጠባበቅ” ዙሪያ የመገናኛ ብዙኃን በሚኖራቸው ሚና ላይ ስልጠና በሰጠበት መድረክ ላይ አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሰረት ነው የሚባለው፤ በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ምርታማ በመሆን፣ ፍጆታዎችን በመጠቀም፣ ትውልድ በማስቀጥል፤ ጥሪት በመፍጠር እና በማከማቸት እንዲሁም ለቀጣዩ ትውልድ በማውረስ ያለውን ወሳኝ ሚና ከግምት በማስገባት ነው። ቤተሰብ የኅብረተሰቡን መልካም እሴቶች በማስተማር የልጆችን ሰብእና የመገንባት፣ አባላቱን ከጥቃት የመጠበቅ፤ ልጆች ወላጆቻቸውን እና ታላላቆቻቸውን የማክበር፣ በአቅማቸው ልክ በሥራ የማገዝና የመታዘዝ ተግባር እንዲፈጽሙ፣ የልጆችን የጤና፣ የተመጣጠነ የምግብ ስርዓት፣ የትምህርት ፍላጎቶችን የማሟላትና የመከታተል፣ በቤተሰብ አባላት መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር የማድረግ፣ ልጆች ወንጀል ነክ ጉዳዮች ውስጥ እንዳይገቡ የመጠበቅና የመከላከል ግዴታዎች አሉበት። ቤተሰብ ይህንን ኃላፊነቱን ሲወጣ ጤናማ ማህበረሰብ እና የሰለጠነ አመለካከት ያለው ትውልድ ይፈጠራል።

ቤተሰብ የማህበረሰብ መሰረት (social unit) በመሆኑ የአንድ ማህበረሰብም ሆነ የሀገር ሁለንተናዊ ነጸብራቅ ነው። በዓለም ታሪክ መነሻውን ቤተሰብ ያላደረገ ግለሰብ፣ ህብረተሰብ እና ሀገር የለም። ሁሉም የሚቀረጸው እና የኋላ ማንነቱን የሚያገኘው ከቤተሰብ ነው። በመሆኑም በአንድ ሀገር ላይ የሚታዩ መልካም ውጤቶችም ሆኑ ውስብስብ ችግሮች መነሻቸው ቤተሰብ ነው።

ሆኖም በሉዓላዊ ተጽእኖ እንደሀገር የቤተሰብ መልካም እሴት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ በመምጣቱ ቤተሰብ ተገቢውን ማኅበራዊ ሚና እየተወጣ ካለመሆኑ በላይ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየተጋለጠ ይገኛል። ወላጆች ተቻችለው ትዳራቸውን መምራት ተስኗቸው ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከመጋለጣቸው ባሻገር ልጆች የሚበተኑበት ሁኔታ በስፋት ይስተዋላል። ልጆች የቤተሰብ ፍቅር እና እንክብካቤ አጥተው በየጎዳናው ለልመና እጃቸውን የሚዘረጉበትና ከትምህርት ገበታቸው የተሰናከሉበት ሁኔታ በስፋት ተፈጥሯል። በዚህም እንደ ሀገር በዘንድሮው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ የተመዘገበው ውጤት አንዱ ማሳያ ነው።

እንዲሁም ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሰረት ብሎም የሀገር ነጸብራቅ ቢሆንም ቅሉ የሚጠበቅበትን ሚና ባለመወጣቱ እንደሀገር የማንወጣው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አዘቅት ውስጥ ገብተናል። በዚህም ጎረቤት ከጎረቤት ተደጋግፎና ተቻችሎ የመኖር የቤተሰብ መልካም ባሕሉ ተሸርሽሮ የአንድ ሀገር ሰዎችና ህዝብ እርስ በርስ ሲገፉፉና ሲጋጩ ይስተዋላል ብለዋል።

እንደ ዓለምም ሴት እና ሴት፤ ወንድና ወንድ የሚጋባበት ሁኔታ በመፈጠሩ የቤተሰብ ቀጣይነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ገብቷል ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ የቤተሰብ ጉዳዮች ሰፊ እና ውስብስብ በመሆናቸው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል። በመሆኑም በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ጉዳይ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላት በተለይ ተጋላጭ ቤተሰቦችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ አገልግሎቶች እንዲደራጁ ተገቢውን እገዛ እና ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ቤተሰብ እና ቤተሰብ ተኮር ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ዓለም አቀፍ የዘላቂ ልማት ግቦችንም ሆነ ሀገራዊ የልማት እቅዶችን ለማሳካት ከፍ ያለ ሚና አላቸው። ስለዚህ ቤተሰብ እንደኅብረተሰብ መሰረትነቱ ተገቢ ሚናውን እንደሀገር መወጣት እንዲችል እንዲሁም የቀደመ መልካም እሴቱ ተጠብቆ በመጤ ባህል ሳይበረዝ ከትውልድ ትውልድ እንዲሸጋገር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሕገ መንግሥቱን መሰረት በማድረግ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አኳያ ከመገናኛ ብዙሃን ተቋማት፣ ከባለድርሻ አካላትና ከሲቪክ ማህበራት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል።

በአጠቃላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቤተሰብ ዙሪያ የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ፣ የአሠራርና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግ፤ የግንዛቤ እና የአድቮኬሲ ሥራዎችን በማከናወን የቤተሰብ መልካም እሴቶች እንዲጠናከሩ እና እንዲጎለብቱ፣ የቤተሰብ መብቶች እንዲጠበቁ፣ ቤተሰብ እና አባላቱ እንደ ህብረተሰብ ዋና መሠረት ተገቢውን አገልግሎት አግኝቶ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙ እንዲገነባ እና ደህንነቱ እንዲረጋገጥ፤ ቤተሰብ የህብረተሰብ መሰረትነቱን (ሶሻል ዩኒት) ተጠቅሞ በሀገር እድገት እና ብልጽግና ውስጥ ተገቢ ሚናውን እንዲወጣ ለማድረግ የአስፈጻሚ አካላት ድርሻ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ይህንን ተፈጻሚ ለማድረግ ለሴክተሩ ከተሰጠው ኃላፊነት በመነሳት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የጋራ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው አቶ ተስፋዬ አሳስበዋል።

## የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/Re-26/2015

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል Hose Assemblies machine /የሆዝ መጭመቂያ ማሽን/ በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላችሁ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዢ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ፡፡ ተጫራቾች በጨረታ ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O ከቴክኒክ ዶክመንቶች ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዢ መምሪያ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው በዕለቱ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በግዢ መምሪያ ይከፈታል፡፡ ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን / ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ
ስልክ 0114420216/ ፋክስ 0114420688
አዲስ አበባ

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን**
**ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

## የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/Re-01/2015

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል ላፕቶፕ፣ ፕሪንተር፣ ኮምፒተር፣ እና አክሰሰሪ፣ ኤር ኮንድሽን የኔት ወርክ እስውቾች በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላችሁ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ሕንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዢ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ፡፡ ተጫራቾች በጨረታ ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O ከቴክኒክ ዶክመንቶች ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዢ መምሪያ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡ጨረታው በዕለቱ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በግዢ መምሪያ ይከፈታል፡፡ ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን/ ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ
ስልክ 0114420216/ ፋክስ 0114420688
አዲስ አበባ

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን**
**ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

## የጨረታ ማስታወቂያ

የባሌ ዞን ገንዘብ ጽ/ቤት ለዞኑ ውሃ፤ ሀብት ልማት ኢነርጂ ጽ/ቤት በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ በስሩ ላሉ 6 /ስድስት/ወረዳዎች ( በርበሬ ጉራ ዳሞሌ ፤ ደሎ መና፤ መደ ወላቡ ፤ ሃረና ቡሉቅ እና ጎሮ ) በቦቴ /በFSR መኪና ውሃ ከተጠቀሱት ወረዳዎች ድረስ ማጓጓዝ ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ፡-**

1. ተጫራቾች በጨረታው ለመካፈል የሚያስችል በሚወዳደሩበት ዘርፍ የተሰማሩበት ተጓዳኝ ሕጋዊ የ2015 የንግድ ፈቃድ ያላቸው፤ ቲን ነምበር ፤ ቫት ፤ በአቅራቢነት የተመዘገቡበትን ሊብሬ እና የኢንሹራንስ ተመዝጋቢ መሆኑን መስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ለጨረታ ማስከበሪያ ብር 30000.00 / ሰላሳ ሺህ ብር/ የያዘ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከጨረታ ሰነድ ጋር ማቅረብ የሚችል፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 100.00 በባሌ ዞን ገንዘብ ጽ/ቤት ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000040165267 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማስገባት ሰነዱን ከቢሮ ቁጥር 15 መወሰድ ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታውን ፋይናንሻል ኦርጅናል ሰነድ ፋይናንሻል ኮፒ ሰነድ እና ቴክኒካል ኦርጅናል ሰነድ በተለያዩ ሶስት ፖስታዎች ውስጥ በማድረግ የድርጅታቸውን ማህተምና ፊርማ፤ ሁሉም ሰነዶቻቸው እና ፖስታ ላይ በመምታትና በመፈረም ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው በማስታወቂያ ከወጣበት የስራ ቀን በ16 ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ባሌ ዞን ገንዘብ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 15 በማስገባት ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4:30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ዕለቱ በአል ወይም ዝግ ከሆነ በቀጣዩ የሥራ ቀን ጨረታው ይከፈታል፡፡
6. የመኪና ቦቴ/ FSR ሞዴል ከ 2015 እና ከዛ ባላይ የቅርብ ጊዜ ሞዴል መሆን አለበት፡፡
7. የመኪና ውሃ ቦቴ/ FSR በትንሹ ከ 12-16$m^3$ ወይም 17-22$m^3$ የመጫን ችሎታ ያለው መሆን አለበት፡፡
8. የሚወዳደርበትን የውሃ ቦቴ/ FSR የባለ ንብረትነት ሊብሬ፤ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
9. የሚወዳደርበትን የውሃ ቦቴ/ FSR ኢንሹራንሱን የተመዘገበበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
10. የሚወዳደርበትን የውሃ ቦቴ/ FSR የቴክኒክ ግምገማ አልፎ የ2015 የታደሰ ቦሎ ማቅረብ የሚችል፡፡
11. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በመሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ ባሌ ዞን ገንዘብ ጽ/ቤት ስ.ቁ 0226650225 /0222440037 ደውለው ይጠይቁ

**የባሌ ዞን ገንዘብ ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/Re-30/2015

በኬሚካል ኢንዱስት ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል Plummer Blocks for conveyor Belt and screw conveyor በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለዚህ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዢ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ:: ተጫራቾች በጨረታ ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2 % የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዢ መምሪያ በተዘጋጀው ሳጥን ስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:: ጨረታው በዕለቱ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በግዢ መምሪያ ይከፈታል፡: ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**ስልክ 0114420216 ፋክስ 0114420688 አዲስ አበባ**

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/Re-28/2015

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል Polyster martine cloth for pneumatic conveyor በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡: ስለዚህ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዢ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ:: ተጫራቾች በጨረታ ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ ብር 2 % የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም C.P.O ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዢ መምሪያ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:: ጨረታው በዕለቱ የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በግዢ መምሪያ ይከፈታል፡: ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**ስልክ 0114420216 ፋክስ 0114420688 አዲስ አበባ**

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

## የቁም ደን ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር OFWE/GU-05/2015
## ስመጀመሪያ ጊዜ የወጣ

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ወለጋ ቅ/ጽ/ቤት ቄለም ወለጋ እና ምስራቅ ወለጋ ዲስትሪክቶች፤ ጅማ ቅ/ጽ/ቤት በለጠ ጌራ ዲስትሪክት፤ ሀረርጌ ቅ/ጽ/ቤት ጀሎ ሙክታር ሃደስ ዲስትሪክት ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ ግንድላ፤ እሉ አባ ቦራ ቅ/ጽ/ቤት ስቦ ቶሊ ቆቦ ገባ-ድዶሰ እና ያዩ ዲስትሪክቶች ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ የ “Pinus patula” እና የ“Grevillea robusta” ግንድላ፤ እንዲሁም አርስ ቅ/ጽ/ቤት ጭላሎ ጋለማ ዲስትሪክት ላይ የፈረንጅ ጥድ እና የባህር ዛፍ ድብልቅ ግንድላ፤ በተጨማሪም አርስ ቅ/ጽ/ቤት ሙኔሳ እና ጋንቦ ዲስትሪክቶች ላይ ተቆርጦ የተዘጋጀ የፈረንጅ ጥድ ግንድላ እና የ“Grevillea robusta" ጥራቱ የቀነሰ ደረቅ ግንድላ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

**ስሁስተኛ ጊዜ የወጣ**

ጅማ ቅ/ጽ/ቤት በብያ ፎላ ዲስትሪክት ላይ የ“Grevillea robusta” ግንድላ፤ በሌ ቅ/ጽ/ቤት አሎሼ ባቱ እና ኩበዩ ዲስትሪክቶች ላይ የፈረንጅ ጥድ እና የባህር ዛፍ ድብልቅ ግንድላ፤ ቦረና ጉጅ ቅ/ጽ/ቤት ቦሬ ዲስትሪክት ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ ግንድላ፤ ወለጋ ቅ/ጽ/ቤት ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዲስትሪክት ላይ የቁም የፈረንጅ ጥድ ግንድላ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም፡-**

1. የግንዲላ እና የእንጨት መሰንጠቂያ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፤ የቫት (VAT) ተመዝጋቢና “TIN Number ያላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም ስለጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ የጨረታ ሰነድ ለእያንዳንዳቸው የማይመለስ 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ቀበና ሼል/ አይል ሊቢያ አጠገብ በሚገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 201 እና ጨረታው በወጣበት ቦረና ጉጅ ቅ/ጽ/ቤት አዶላ ከተማ፤ ጅማ ቅ/ጽ/ቤት ጅማ ከተማ፤ በሌ ቅ/ጽ/ቤት ጎባ ከተማ፤ አርስ ቅ/ጽ/ቤት ነጌሌ አርስ ከተማ፤ ወለጋ ቅ/ጽ/ቤት ጊምብ ከተማ፤ ሀረርጌ ቅ/ጽ/ቤት ጭሮ ከተማ እና ኢሉ አባ ቦራ ቅ/ጽ/ቤት መቱ ከተማ በመግዛት በጨረታው መሣተፍ ይችላሉ፡፡
2. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው ለ15 ተከታታይ ቀናት ሲቆይ ለሁለተኛ ጊዜ የወጣው ደግሞ ለ10 ተከታታይ ቀናት ይቆያል፡፡
3. ጨረታው የሚዘጋበት እና የሚከፈትበት ትክክለኛው ቀንና ሰዓት በጨረታውሰነድ ውስጥ ይገለጻል፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና(Bid bond) የሚሆን ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ 5% በማስላት በድርጅቱ ዋና መ/ቤት የምትጫረቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች በቅ/ጽ/ቤት የምትጫረቱ መ/ቤቱ ከሚገኝበት ከተማ በባንክ በተረጋገጠ ደረሰኝ (CPO)ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
5. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0111240249 በመደወል መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት**

# ስፖርት

## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በስፔን ግማሽ ማራቶን ክብረወሰን አሻሽለው አሸነፉ

**ብርሃን ፈይሳ**

በፈረንጆቹ የጥቅምት ወር መጀመሪያ ከሚካሄዱ የግማሽ ማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ በስፔን የሚካሄደው የግራኖለር ግማሽ ማራቶን ሩጫ ነው። በስፔኗ ባርሴሎና አስተናጋጅነት የሚካሄደው ይህ የሩጫ ውድድር መነሻውን እአአ በ1987 የሚያደርግ ሲሆን፤ በየዓመቱ እየተከናወነ ከዚህ ደርሷል። ኢትዮጵያዊያን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ አትሌቶችን የሚያሳትፈው ይህ ውድድር በወንዶች ኢትዮጵያዊው ጀግና አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ እአአ በ2005 እና 2006 በተከታታይ አሸናፊ በመሆኑ በተለየ መልኩ ይታወሳል። በሴቶች በኩልም እአአ በ2006 አንጋፋዋ አትሌት ጌጤ ዋሚ አሸናፊ ከመሆኗ ባለፈ በወቅቱ ያስመዘገበችው 1:10:24.2 የሆነ ሰዓት እስካሁንም ድረስ ሊደፈር ያልቻለ የቦታው ክብረወሰን በመሆን ዓመታትን አስቆጥሯል።

በዚህ ውድድር ያለፉትን ዓመታት በተለይ ኬንያዊያን አትሌቶች የበላይ ሆነው ቢቆዩም ከትናንት በስቲያ በተካሄደው ውድድር ላይ ግን የበላይነቱ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ መመለሱ ተረጋግጧል። 10ሺ ሯጮች የተካፈሉበት ይህ ውድድር በወንዶች በኩል ኢትዮጵያዊው አትሌት ሃጎስ ገብረህይወት የስፍራውን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር አሸንፏል። በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከአንድ እስከ ሶስት ያለውን ደረጃ ይዘው በመፈጸም የበላይነቱን መውሰዳቸውን ማይ ቤስት ራንስ የተሰኘው ድረገጽ አስነብቧል።

በዚህ የግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ ከተካፈሉ ታዋቂ አትሌቶች መካከል አንዱ ኬንያዊው ሳሙኤል ዋንጂሩ ነው። ይህ አትሌት እአአ በ2008 እና 2009 የዚህ ውድድር አሸናፊ ሲሆን፤ በመጀመሪያ ተሳትፎው ርቀቱን 59ደቂቃ ከ26 ሰከንዶች በመሸፈን ነበር በስፍራው አዲስ ሰዓት ያስመዘገበው። ይህም ክብረወሰን ለ15 ዓመታት የሚያሻሽለው አትሌት ሳይገኝ ቆይቷል። በዘንድሮው ውድድር ግን ኢትዮጵያዊው አትሌት ሃጎስ በአንድ ደቂቃ ፈጥኖ በመግባት የስፍራውን ክብረወሰን የግሉ ማድረግ ችሏል። በሪዮ ኦሊምፒክ በ5ሺ ሜትር የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት የሆነው ሃጎስ ከጉዳት ጋር በተያያዘ ባለፉት ዓመታት በውድድሮች እምብዛም ሳይታይ ቆይቷል።

በሞስኮ እና ቤጂንግ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች ላይ በሚታወቅበት ርቀት የብር እና የነሃስ ሜዳሊያዎችን የግሉ ማድረግ የቻለው ሃጎስ፤ በተለይ የሚታወቀው በመም ሩጫዎች ላይ ነበር። በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጀመሪያ በጎዳና ላይ ሩጫ ዳግም በአዲስ ብቃት ወደ ውድድር መመለሱን ያስመሰከረው አትሌቱ ሩጫውን በአሸናፊነት አጠናቋል። የስፍራውን ክብረወሰንም ያሻሻለው 58ደቂቃ ከ55 ሰከንዶች በመግባት ነው። ይህም አትሌቱን በውድድሩ ታሪክ ከ1ሰዓት በታች በመግባት ሁለተኛው አትሌት ያደርገዋል። አትሌቱን ኬንያውያን ተከትለውት የገቡ ሲሆን፤ ኤድመንድ ኪፕኔጌቲች እና ነሂሚሃ ኪፕዬጎን ሁለተኛ እና ሶስተኛ ሆነዋል። ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ብርሃኑ ታርቶ ደግሞ በአራተኛነት ውድድሩን ሊፈጽም ችሏል።



በወንዶች የክብረወሰን ባለቤት የሆነው አትሌት ሃጎስ ገብረህይወት፤

በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ውድድሩ በፈጣን ሰዓት ተደምድሟል። ውድድሩ ሶስት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተከታትለው የገቡበት ሲሆን፤ በሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት እጅ የነበረው ክብረወሰን የተሰበረበትም ነበር። ሩጫውን አጠናቃ በቀዳሚነት የገባቸው አትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ 1:06:40 የሆነ ፈጣን ሰዓት አስመዝግባለች። አትሌቷ በሃገሯ ልጅ ከተያዘው ሰዓትም አራት ደቂቃ ፈጥና በመግባት አስደናቂ ብቃቷን አስመስክራለች።

በጠባብ ደቂቃዎች ልዩነት ትዕግስትን ተከትለው የገቡት የሃገሯ ልጆችም ያስመዘገቡት ሰዓት በተመሳሳይ ፈጣን በመሆኑ ከዚህ በኋላ በስፍራው ሰዓት ማሻሻልን አዳጋች ሊያደርገው እንደሚችልም የሚገመት ነው። በሁለት ደቂቃ ዘግይታ በመግባት ሁለተኛ የሆነችው አትሌት ቤተልሄም አፈንጉስ ስትሆን፤ ሩጫዋን የፈጸመችበት ሰዓትም 1:08:08 ሆኗል። በግማሽ ማራቶን ሩጫዎች ልምድ ያላት ይህች አትሌት ባለፈው ዓመት የማድሪድ ግማሽ ማራቶን ውድድርን በሶስተኛነት ደረጃ ነበር ያጠናቀቀችው። ሌላኛዋ አትሌት አዲሴ አንዷለም ደግሞ 1:09:34 በሆነ ሰዓት በመግባት የሶስተኛነት ደረጃን መያዝ ችላለች።



# በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

## የግዥው መለያ ቁጥር አአከመባ/ግብዓት/ቡ-1/004-5/2015

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን በ2015 በጀት ዓመት ለመንገድ ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ከታች የተገለፁትን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች በሰዓት የኪራይ አገልግሎት ግዥ በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | በሰዓት ለኪራይ የተፈለገ የማሽነሪ ዓይነት | የስራት ዘመን እ.ኤ.አ (GC) | ብዛት በቁጥር | አጠቃላይ ለኪራይ የሚፈለገው ሰዓት | የጨረታ መለያ ቁጥር | ጨረታ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ | የጨረታ መዝጊያ ቀንና ሰዓት | የጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት | የጨረታ ማስከበሪያ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dozer (≥300 Hp) | ≥2012 GC | 2 | እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 .ም | አአከመባ/ግብዓት/ቡ-1/004-5/2015 | 60 ቀን | የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት 8፡30 | የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት 8፡45 | ለአንድ ማሽነሪ 10,000 (አስር ሺህ ብር) |
| 2 | Motor Grader (≥140 Hp) | ≥2012 GC | 2 | | | | | | |
| 3 | Chain Excavator (Bucket) (≥1.5m³ heaped and ≥170Hp) ≥2012 GC | ≥2012 GC | 2 | | | | | | |
| | Chain Excavator (≥1.6m³ heaped and 200Hp) (Bucket) | ≥2012 GC | 2 | | | | | | |
| 4 | Chain Excavator (Jack Hammer) >200 Hp, for jack hammer min. operating weight shall to be≥2500 kg and min. impact rate shall to be ≥ 350 | ≥2012 GC | 2 | | | | | | |
| 5 | Wheel Loader ≥ 3m³ Bucket capacity and ≥180Hp) | ≥2012 GC | 4 | | | | | | |
| 6 | Wheel Excavator ≥ 1M³ Bucket capacity and 135 HP | ≥2005 GC | 4 | | | | | | |
| 7 | Double Drum Roller 4 ton | ≥2008 GC | 3 | | | | | | |
| 8 | Pneumatic Roller ≥12 ton (Unballasted ) | ≥2008 GC | 2 | | | | | | |
| 9 | Asphalt Paver (paving width ≥2.5m without screed, Engine capacity >150 hp, wheeled/chain drive) | ≥2005 GC | 2 | | | | | | |
| 10 | Asphalt Distributer (≥6000 liter Tanker Capacity, ≥2m Spraying Width, Engine Capacity ≥150 hp | ≥2005 GC | 1 | | | | | | |
| 11 | Water trucks ≥13,000Lit. | ≥2010 GC | 1 | | | | | | |

**ስለዚህ ከ1-11 በተገለፀው መሰረት**

1. ተጫራቾች አግባብነት ያለው ለዘመኑ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣ አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከአዲስ አበባ ከተማ ኮንስትራክሽን ቢሮ፤ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት እና በጨረታ መወዳደር የሚያስችል የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ታክስ ክሊራንስ ሰርትፍኬት እንዲሁም በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድህረ ገፅ (WWW.PPA.gov.et) የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መመዝገብ ያኖርባቸዋል።
በተጨማሪም ተጫራቾች በሰዓት ለኪራይ አገልግሎት ለሚወዳደሩባቸው የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ወይም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ /ውልና ማስረጃ/ የተረጋገጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ውክልና ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ክፍል 6 /ስድስት/ አባሪ ሁለት በቀረበው ቅፅ መሰረት በማረጋገጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ መጀመሪያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከባለሥልጣኑ መ/ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 135 መውሰድ ይችላሉ።
3. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ዋስትናው ከታወቀ ባንክ በባንክ ጋራንቲ ወይም በ Certified Payment Order (CPO) ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል። በተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ተጫራቾች ባቀረቡት የማሽነሪ ብዛት መጠን የሚወሰን ሲሆን፣ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተፈለገውን የማሽነሪ ብዛት በሙሉ የሚያቀረቡት የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከላይ በሰንጠረዥ በተገለፀ መሰረት ይሆናል። ከባንክ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) ለ120 ቀናት ፀንቶ የሚቆይ መሆን ይኖርበታል።
4. ማንኛውም ተጫራች የመጫረቻ ሰነዱን በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ከላይ በሰንጠረዥ የጨረታ መዝጊያ ተብሎ እስከ ተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 1o9 በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ከላይ በሰንጠረዥ የጨረታ መክፈቻ ተብሎ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ይከፈታል። መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

(ሳርቤት ፑሽኪን አደባባይ አጠገብ)
ስልክ ቁጥር 011-3-71-41-03 /011-3-72-28-15

# የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን